# የዓለምን ከንቱነት የሚሰብኩ የዐማርኛ ቃለ ግጥሞች

**መስፍን መሰለ**

## አኅጽሮተ ጥናት

የዓለምን ከንቱነት የሚሰብኩ የዐማርኛ ቃለ ግጥሞች፣ ዘገየም ፈጠነ ሞት የኹሉም ሰው ዕጣ ፈንታ መኾኑን ይሰብካሉ፡፡ ከሞት በኋላም ሰው ዘለዓለማዊ ሕይወትን ይወርስ ዘንድ በሕይወተ ሥጋ እያለ ለሕይወተ ነፍስ እንዲተጋ ያሳስባሉ፡፡ በክርስትና እምነት የነፍስ ከሥጋ መለየት የመጀመሪያ ሞት ነው፡፡ ይኽ ዓይነቱ ሞትም እንደ ማንቀላፋት ይቆጠራል፡፡ ከሥጋ ሞት በኋላ ትንሣኤ ስላለ ሰው በሥጋው ሲሞት ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለች፣ ፍርድንም ትቀበላለች፡፡ በመኾኑም፣ ሰው ሞተ ነፍስ እንዳይደርስበት ሃይማኖታዊ ሕግን በማክበር፣ በእምነት በመኖር፣ ምጽዋት በመስጠት፣ ፈቃደ ሥጋን በመተው ከኹለተኛ ሞት እንደሚድን ቃለ ግጥሞቹ ይሰብካሉ፡፡ እንዲኽ ዓይነት መልእክት የሚተላለፍባቸው ቃለ ግጥሞች በደስታና በኀዘን አጋጣሚዎች በልዩ ልዩ መንገድ ይቀርባሉ፡፡

ይኽን ጥናት ማካኼድ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በተጠቀሱት መልእክቶች ላይ ትኩረት በሚያደርጉ የዐማርኛ ቃለ ግጥሞች ላይ የተደረገ ጥናት አለመኖርና ክፍተቱን ለማጥበብ ምርምር ማድረግ አስፈላጊ በመኾኑ ነው፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የዓለመ ሕይወትን ከንቱነት የሚሰብኩ የዐማርኛ ቃለ ግጥሞችን መመርመር ነው፡፡ ከዚኽ የሚመነጩ ዝርዝር ዓላማዎችም፡- የሞትን አይቀሬነትና የሀብተ ሥጋን ቀሪነት የሚያስገነዝቡ፣ ከሞተ ነፍስ ለመዳን መመነንን የሚያበረታቱ፣ ሃይማኖታዊ ምግባር መፈጸም አስፈላጊ መኾኑን የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞችን መመርመር የሚሉት ናቸው፡፡ ይኽ ጥናት ኅብረተ ሰቡ ስለ ሕይወተ ሥጋና ሕይወተ ነፍስ ያለውን ግንዛቤ በአጠቃላይ ንጽረተ ዓለሙንና የንጽረተ ዓለሙን መነሻ ምክንያቶች፣ እንዲሁም፣ በኅብረተ ሰቡ የዕለት ተለት ሕይወት ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ለመረዳት የሚጠቅም ከመኾኑም ባሻገር ወደ ፊት ለሚደረጉ ተመሳሳይ ጥናቶች እንደ መነሻ ሊያገለግል ይችላል፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከተለያዩ ጽሑፎችና ከሀገር ሽማግሌዎች ነው፡፡ ቃለ ግጥሞቹ ለትንተና የተመረጡት ዓላማ ተኮር ናሙናን (purposive sampling) መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ቁልፍ ቃላት፡- ዓለም፣ ሕይወተ ሥጋ፣ ሕይወተ ነፍስ፣ ምነና፣ ምንኩስና፣ ምጽዋት፡፡

፩) መግቢያ

የሰው ልጅ በሕይወተ ሥጋ ሲኖር ለሥጋው ምቾትና ድሎት የሚሰጡትንና ሥጋዊ እርካታ የሚያገኝባቸውን ጉዳዮች ለማግኘት መጓጓቱና ማግኘቱ ጥቅም እንደሌለው በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞች በርካታ ናቸው፡፡ ቃለ ግጥሞቹ ሰው የዓለምን ኑሮ እንዲንቅና እንዲተው፣ መንግሥተ ሰማይን በመውረስ ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዲኖር የሚያስችለውን መንገድ እንዲከተል ይቀሰቅሳሉ፤ ይሰብካሉ፡፡ የዓለምን ከንቱነትና የሞተ ሥጋን አይቀሬነት የሚያስረዱና የሰው ልጅ ከኹለተኛ ሞት ለመዳን ዓለምንና በውስጡ ያለውን ኹሉ እንዲንቅና ከሕግ የወጣ ክፉ ሥራ እንዳይሠራ የሚሰብኩ የዐማርኛ ቃለ ግጥሞች በኅብረተ ሰቡ ዘንድ በደስታና በኀዘን አጋጣሚዎች በልዩ ልዩ መንገድ ይቀርባሉ፡፡ የመዲና እና የዘለሰኛ (የለቅሶ፣ የልመና) ቃለ ግጥሞች የሚቀርቡባቸው አጋጣሚዎች የዓለማዊ ሕይወትን ከንቱነት፣ የዓለመ ዘላለምን አስፈላጊነት መስበክ የተለመደ ነው፡፡ በመዝሙረ ፍልሰታም ተመሳሳይ መልእክት ይነገራል፡፡

ከዘለሰኛ ግጥሞች አንዱ በኾነው በለቅሶ ግጥም አማካኝነት የዓለማዊ ሕይወት ከንቱነቱ ተዘውትሮ ይሰበካል፡፡ የሰው ልጅ ለሕይወተ ሥጋው የወጣ የወረደበትን፣ የደከመበትን፣ ያፈራውን ሀብትና ንብረት፣ እንዲሁም፣ ቤተ ሰቡን ጥሎ ማለፉን ወይም በለጋ ዕድሜው በመቀጨቱ፣ በባህሉ መልካም የሚባለውን ነገር ሳይፈጽም በማለፉ ይታዘናል፡፡ በሞት አጋጣሚ በሚደረደረው የለቅሶ ግጥምም ለሕይወተ ሥጋ ፍላጎት የሚደረገውን ጥረት ያጣጥላል፤ ለሕይወተ ነፍስ ማሰብና መድከም ተገቢ መኾኑን ይሰብካል፡፡ እንደዚሁም፣ ለማኞች የተለማኙ ልቦና እንዲራራና እጁን በልግስና ለምጽዋት እንዲዘረጋ ለማድረግ የሚደረድሯቸው ቃለ ግጥሞች ሕይወተ ሥጋን ዝቅ፣ ሕይወተ ነፍስን ከፍ ያደርጋሉ፡፡ ምጽዋት መስጠት ለሕይወተ ነፍስ ዋጋ እንዳለው ይሰብካሉ፡፡

በተለያዩ (የመዲና፣ የዘለሰኛ፣ የለቅሶ፣ የልመና ወዘተረፈ) ቃለ ግጥሞች የዓለማዊ ሕይወት ከንቱነት ተዘውትሮ ይሰበካል፡፡ የሰው ልጅ ለሕይወተ ሥጋው የወጣ የወረደበትን፣ የደከመበትን፣ ያፈራውን ሀብቱንና ንብረቱን፣ ቤተ ሰቡን ጥሎ ማለፉን ወይም በለጋ ዕድሜው በመቀጨቱ በባህሉ መልካም የሚባለውን ነገር ሳይፈጽም በማለፉ ይታዘናል፡፡ በመዲናና በዘለሰኛ ግጥሞች መንፈሳዊ ጉዳይ ይሰበካል፤ ኀዘንና ትካዜ ይነገራል፡፡

በሞት አጋጣሚ በሚደረደረው የለቅሶ ግጥምም ለሕይተ ሥጋ ፍላጎት የሚደረገውን ጥረት ያጣጥላል፤ ለሕይወተ ነፍስ ማሰብና መድከም ተገቢ መኾኑን ይሰብካል፡፡ ለማኞች የተለማኙ ልቦና እንዲራራና እጁን በልግስና ለምጽዋት እንዲዘረጋ ለማድረግ የሚደረድሯቸው ቃለ ግጥሞች ሕይወተ ሥጋን ዝቅ፣ ሕይወተ ነፍስን ከፍ ያደርጋሉ፡፡ ምጽዋት መስጠት ለሕይወተ ነፍስ ዋጋ እንዳለው ይሰብካሉ፡፡

ይኽን ጥናት ማካኼድ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በተጠቀሱት መልእክቶች ላይ ትኩረት በሚያደርጉ የዐማርኛ ቃለ ግጥሞች ላይ የተደረገ ጥናት አለመኖርና ክፍተቱን ለማጥበብ ምርምር ማድረግ አስፈላጊ በመኾኑ ነው፡፡

የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የዓለመ ሕይወት ከንቱነትን የሚሰብኩ የዐማርኛ ቃለ ግጥሞችን መመርመር ነው፡፡ ከዚኸ የሚመነጩ ዝርዝር ዓላማዎችም፡- ፩) የሞትን አይቀሬነትና የሀብተ ሥጋን ቀሪነት የሚያስገነዝቡ፣ ፪) ከሞተ ነፍስ ለመዳን መመነንን የሚያበረታቱ፣ ፫) ሃይማኖታዊ ምግባር መፈጸም አስፈላጊ መኾኑን የሚሰብኩ፣ ፬) ገዳም መግባት አስፈላጊ መኾኑን የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞችን መመርመር የሚሉት ናቸው፡፡

ይኽ ጥናት ኅብረተ ሰቡ ስለ ሕይወተ ሥጋና ሕይወተ ነፍስ ያለውን ግንዛቤ በአጠቃላይ ንጽረተ ዓለሙንና የንጽረተ ዓለሙን (world view) ምክንያቶች፣ በኅብረተ ሰቡ የዕለት ተለት ሕይወት ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ለመረዳት ያገለግላል፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚደረደሩ ቃለ ግጥሞች ስለ ሕይወተ ሥጋና ስለ ሕይወተ ነፍስ ምን እየተባለ እንደሚገለጽ ለመረዳት ያስችላል፡፡ ወደ ፊት ለሚደረጉ ተመሳሳይ ጥናቶች እንደ መነሻ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ለዚኽ ጥናት የሚያስፈልጉት መረጃዎች የተሰበሰቡት ከመጻሕፍትና የቃል መረጃ ከሰጡ ሰዎች ነው፡፡ መጻሕፍቱም፣ *የአማርኛ ሐረግ* (ዓለማየሁ ሞገስ፣ ፲፱፻፷፯)፤ *የአማርኛ ግጥምና ቅኔ፤ ማስተማሪያ* (ዓለማየሁ ሞገስ፣ ፲፱፻፶፬)፤ *አማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው* (ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ፲፱፻፷፩)፣ *ዝክረ ነገር* (ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ፲፱፻፷፩)፣ *ያማርኛ ሐረግ በቅኔዎች ሕግ* (ተገኝ ተአምሩ፣ ፲፱፻፷፩) እና *ንባብ ወትርጓሜ ዘቅኔያት፡፡ አዕማደ ምስጢራት* (ይኄይስ ወርቄ፣ 1968) (እ.ኤ.አ.)፣ *የቅኔ አፈታት ዘዴዎችና የምርጥ ቅኔዎች ስብስብ* (ንጉሴ ነገዎ ደጋጋ፣ 1992) እና *አዲሱ የአማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው* (ደበበ ኃይለጊዮርጊስ፣ 2008) ናቸው፡፡ መጻሕፍቱ የተመረጡት ለጥናቱ የሚረዱ መረጃዎች እንዳላቸው በንባብ በመረጋገጡ ኾን ተብሎ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥቂት በቃለ ግጥም ላይ ትኩረት ያደረጉ የመመረቂያ ጥናቶች በመረጃ ምንጭነት አገልገለዋል፡፡ ዓላማ ተኮር ናሙናን (purposive sampling) መሠረት በማድረግ ለትንተና የተመረጡት ቃለ ግጥሞች የተወሰዱት *አማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው* ከሚለው ከማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩) መጽሐፍ ነው፡፡ ይኽም የተደረገበት ምክንያት ከሌሎቹ ሥራዎች በመሻሉና የአንዳንዶቹ ሥራዎች መሠረት ኾኖ በመገኘቱ ነው፡፡

ስለ ዐለም ከንቱነት የተደረደሩ ቃለ ግጥሞችን ከመመልከታችን በፊት የቃለ ግጥም ባሕርያትን በተለይም ተለዋዋጭነትን ትኩረት ሰጥተን እንመለከታለን፡፡ ለተለዋዋጭነት ትኩረት መስጠት ያስፈለገበት ምክንያት ለትንተና በተመረጡት ቃለ ግጥሞች ላይ የሚታየውን መለዋወጥ ቀድሞ መረዳት መደናገርን ያስቀራል በሚል እምነት ነው፡፡ ይኽንንም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

**፪) ምነናን የሚሰብኩ መዲናና ዘለሰኛ ቃለ ግጥሞች**

ምነናን የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞችን ከመመልከታችን በፊት የምነናን ምንነት መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ይኽንንም ከቃሉ የመዝገበ ቃላት ፍቺ በመጀመር እንመለከታለን፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል (፲፱፻፺፫፤ ፶፯) ምነና ለሚለው ስም የተሰጠው ፍቺ “የዓለምን ነገር፣ ተድላ ደስታን ንቆና ትቶ ከሰው በመለየት፣ በዱር፣ በጫካ ወይም በገዳም መኖር” የሚል ነው፡፡ ለቃሉ መፍቻ ከተደረደሩት መካከል “የዓለምን ነገር ንቆና ትቶ” የሚለው ሐረግና

ገዳም የሚለው ቃል የሚገልጹዋቸውን እሳቤዎች ማስረዳት የምነናን ምንነት በተሻለ ደረጃ ለመረዳት ያስችላል፡፡ ገዳም የሚለው ቃል ከሚገልጸው እሳቤ እንጀምር፡፡

ገዳም "መነኰሳት ከዓለማዊ ኑሮ ተገልለው በሃይማኖታዊ ሥርዓትና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተ ክርስቲያን ያለበት ቦታ" ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫ ፤ ፫፻፺)፡፡ ገዳም መግባት፣ ዓለማዊ ኑሮን ትቶ መንፈሳዊ ኑሮን ለመኖር በገዳም ውስጥ መቀመጥ፣ መመነን ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫፤ ፫፻፺)፡፡

ገዳም መግባት የሚቻለው፣ ከኹለት መንገዶች በአንደኛው ነው፡፡ አንደኛው ቀድሞ በመመንኰስና ወደ ገዳም በመኼድ የገዳሙ ማኅበረ ሰብ አባል ለመኾን የገዳሙን አበምኔት በመጠየቅና በማስፈቀድ ነው፡፡ ኹለተኛው፣ የገዳሙ አባል መኾን ወይም ቀድሞ ሳይመነኩሱ ወደ ገዳሙ በመኼድ ለመመንኰስ መወሰንን ለገዳሙ ኃላፊ አሳውቆ የሚሰጠውን የአመክሮ ጊዜ በሚገባ በመፈፀም፣ መንኩሶ ሙሉ የገዳሙ አባል መኾን ነው፡፡

"እጸድቅ ያለ መንኩሶ፣ እካስ ያለ ታግሶ" እንደሚባለው ወደ ገዳም መግባት የሚፈልግ ሰው (ወንድ ወይም ሴት)[1] ፈጥኖም ኾነ ዘግይቶ መመንኰስ አለበት፡፡ የመነኰሰ ሰው ደግሞ የምድራዊውን ዓለም ደስታና ድሎት በቃኝ ያለ፣ ከፍትወተ ሥጋ የተገለለና የአመክሮ ጊዜውን በሚገባ ተወጥቶ የተጸለየበት ወይም የተባረከ ቆብ የጫነ፣ ለነፍሱ ብቻ ያደረ ሰው" (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫፤ ፶፮) ማለት ነው፡፡ በፍትሐ ነገሥት (፲፱፻፷፱፣ ፻፺፫) ስለ ምንኩስና የሚከተለው ተብሷል፡፡

> ...ምንኩስናስ የመሐሢዊት ሕግ ጥበብ ናት፡፡ መነኰሳትም ምድራውያን መላእክት፣ ሰማያውያን ሰዎች ናቸው፡፡ እንደችሎታቸው መጠን የክርስቶስ ተከታዮች በሥራቸውም ሁሉ የሐዋርያት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ከዓለም ፍጥረት በመለየት ፈቃደ ሥጋን በመተው እስከ ሰውነታቸው ድረስ ሥራውን ሁሉ በመናቅ ስለ ትእዛዙ ስለ ፍቅሩ ፈቃዱን ለመፈጸም ያዘዛቸውን ትእዛዝ ስለ ሚያደርጉ እርሱንም ብቻ ከአባቶች፣ ከልጆች፣ ከሚስት፣ ከገንዘብ ይልቅ ፈጽሞ ስለሚወዱ ነው፡፡ ዛሬ በፈቃዳቸው ከሚሠሯቸው ድካም ዕረፍት ስለማድረግ በኋለኛውም ዓለም ፍርድ ፈጽሞ ስለመዳን ብፁዓን ናቸው፡፡ ብፁዓን ግን በፈቃዳቸው ስለሚሠሩት ስለ ኃላፊው ድካም የመንግሥተ ሰማያት ማደሪያ ስለተዘጋጀላቸው ፈጽሞ ብፁዓን ናቸው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ "ከኔ ይልቅ አባቱንና እናቱን የወደደ ለእኔ ሊኾን አይገባም አላቸው፣ ከኔም ይልቅ ወንድ ልጁንና ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊኾን አይገባም፣ የሞቱን መስቀል ተሸክሞ ያልተከተለኝ ለእኔ ሊኾን አይገባም" (ማቴ. ፲ ፣ ፴፯ - ፴፰) የተባለውን ከምንኩስና ሕይወት ጋር የሚያያይዙ አሉ፡፡ ይኽ ዓይነቱ ትርጓሜ ምንኩስና

[1] ወንድና ሴት መነኰሳት በአንድ ገዳም ውስጥ እንዲኖሩ የተፈቀደ አይደለም፡፡ በዚኽም ምክንያት፣ በአንዳንድ ገዳማት ሴት ለብቻ ወንድ ለብቻ፣ በሌላ አካባቢ ደግሞ፣ በአንድ አካባቢ በሚገኙ የተለያዩ ገዳማት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ አንዳንድ የወንድ ገዳማት ሴት ኀብኚ አይገባባቸውም፡፡ እንደዚሁም፣ አንዳንድ የሴት ገዳማት ወንድ ኀብኚ አይገባባቸውም፡፡

የተመረጠ የምእመናን ተግባር መኾኑን የሚያምኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ምእመናን በርካታ እንዲኾን አድርጓል፡፡

ምንም እንኳን የመነኰሰ ኹሉ ወደ ገዳም ይገባል ባይባልም ምንኵስና ለነፍስ ዋጋ ያስገኛል ተብሎ ግን ይታመናል፡፡ ስለኾነም፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ተከታዮች ወደ ምንኵስና በኹለት መንገድ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ "ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ብለው ራሳቸውን ጃንደረባ ያደረጉ አሉ" (ማቴ. ፲፱፣ ፲፪) እንደተባለው ኹሉ ድንግልናቸውን እንደጠበቁ በመመንኰስ ሕይወታቸውን የሚመሩ አሉ፡፡ በሌላ በኩል፣ "ስለ እኔ ሚስቱን የተወ የዘለዓለም ሕይወት አለው" (ማቴ. ፲፱ ፡ ፳፱ - ፴) እንዳለው ኹሉ፣ ሚስት አግብተው ሚስቶቻቸውን በሕይወተ ሥጋ የተለዩ ሰዎች ሊመነኵሱ ይችላሉ፡፡ "ሚስቶቻቸውን በፈቃዳቸው ትተው የመነኰሱ ሰዎች እንደ እግዚአብሔር መላእክት ይሆናሉ" (ማቴ. ፳፪ ፡ ፳፱ - ፴) ተብሎ ይታመናል፡፡

ትዳር መሥርተው ዓለማዊ ኑሮን እየመሩ ከቆዩ በኋላ በተለያየ ምክንያት ወደ ምንኵስና ሕይወት የሚገቡ ምእመናን ብዙ ናቸው፡፡ የትዳር ጓደኛውን በሞት የተነጠቀ ሰው ሌላ ማግባቱን ትቶ ሊመነኵስ ይችላል፡፡ በትዳር መቀጠል ያልቻሉ ባልና ሚስትም ትዳራቸውን አፍርሰው አንደኛቸው ወይም ኹለቱም መመንኰስ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ሌላ፣ ባልና ሚስት ዕድሜአቸው በመግፋቱ ምክንያት መንኵሰው በአንድ ቤት ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

ምንኵስና አስፈላጊ ስለኾነበት ምክንያት ፍትሐ ነገሥት (፲፱፻፷፪፣ ፻፮ - ፻፯) እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

> ሚስት የሌለችው እግዚአብሔርን እንዴት ደስ በሚያሰኘው ገንዘብ እግዚአብሔርን ለማገልገል ያስባልና፣ ሚስት ያለችው ግን ሚስቱን ደስ በሚያሰኛት ገንዘብ ለዓለሙ ሥራ ያስባልና፣ ባገቡትና ባላገቡት መካከል ግልጥ ልዩነት አለና፣ ባል ያላገባች ሴት ወደ እግዚአብሔር በሚያቀርባት ገንዘብ ትተጋለች፣ በሥጋዋና በነፍሷም ንጽሕት ትሆን ዘንድ፣ ባል ያላት ሴት ግን ባሏን እንዴት አድርጋ ደስ በምታሰኘው ገንዘብ ለዚህ ዓለም አኗኗር ታስባለች፡፡ ሰውነቱን ገዝቶ ድንግልናውን ሊጠብቅ የወደደ ግን ፈጽሞ በጎ ሥራ ሠራ፡፡

አንድ ሰው መንኵሶ ገዳም የሚገባ ከኾነ በዓለማዊ ኑሮ ይኖር በነበረበት ጊዜ ያፈራውን ንብረት ኹሉ ለገዳሙ ያስረክባል፡፡ ነገር ግን፣ በእሱ ሥር ይተዳደሩ የነበሩ ልጆች ካሉት ንብረቱን ለእነሱ ያወርሳል፡፡ ስለኾነም፣ የመነኰሰ ሰው ገንዘቡንና የዓለምን ፈቃድ በመተው ማቅ ወይም ወይባ በመልበስ ወገቡን በቀበቶ ታጥቆ በገዳም ይኖራል፡፡ በተለያየ ምክንያት ማቅ ወይም ወይባ ለመልበስ አቅሙ አልፈቅድ ያለ ሰው ግን ማንኛውም ሰው የሚለብሰውን ሱሪም ኾነ እጀ ጠባብ እንዲኹም ጋቢ ወይም ነጠላ መልበስ ይችላል፡፡

አንድ ሰው መንኩሶ ወደ ገዳም ከገባ በኋላ ምግብን መቀነስ፣ ለዘለዓለሙ ሥጋ መብላትን መተው፣ ምክንያት ከሌለው በቀር ወይን መጠጣት አይፈቀድለትም፡፡ "ሕይወቱን ኹሉ ለጾም፣ ለጸሎት፣ ለድካም (በስግደት)፣ ለሥራ" ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ዘወትርም እግዚአብሔርን ለማሰብ፣ መጻሕፍትን ማንበብ፣ ትርጓሜአቸውን ማወቅ፣ የቅዱሳኑን ገድል በማንበብም እነሱን መምሰል ይኖርበታል፡፡ ከበጎ ሥራ በቀር በአእምሮው ክፉ ነገር ማሰብ፣ በአንደበቱም የማይገባውን መናገር አይገባውም፡፡ በአጠቃላይ ለነፍስ ጥቅም ከሌለው ነገር ኹሉ ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል (ፍትሐ ነገሥት ፣ ፲፱፻፷፪)፡፡

አንድ ሰው ከመነኰሰ በኋላ ሥጋዊ ሕይወት የሚፈቅደውን ነገር ለማድረግ ሲባል የሚሰጠውን ዓለማዊ ሹመት መቀበል ተገቢ አይደለም፡፡ በቆሞሱ[2] ትዕዛዝ የገዳሙ መነኰሳት በላያቸው ላይ መምህር (አበ ምኔት) አድርገው ቢሾሙት ግን የተፈቀደ ነው፡፡ በገዳም ከሚኖሩት መነኰሳት መካከል በሃይማኖቱ የተመሰገነውን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራውን መነኩሴ፣ የገዳሙን ሕግ የሚያውቀውንና ማስተዳደር የሚችለውን የገዳሙ አስተዳዳሪ ወይም አበ ምኔት ማድረግ ይቻላል፡፡ አበ ምኔት ለቆሞሱ፣ ቆሞሱም ለኤጲስቆጶሱ[3] ይታዘዛሉ፡፡ የገዳሙ አስተዳዳሪ እንዲኾን የሚመረጠው አበ ምኔትም የገዳሙን ሕግጋት ያወቀ፣ ከተቻለም በውስጡ ያደገ እንዲኾን ይጠበቃል፡፡ አበ ምኔቱ መነኰሳቱንና ገዳሙን የሚመለከቱ ማናቸውንም ዓይነት ጉዳዮች በበላይነት ይመራል፡፡ አመራሩም እንደ ገዳሙ ዓይነት ይለያያል፡፡ በአንዳንድ ገዳማት ክልል ከመነኰሳቱ በተጨማሪ፣ ዓለማዊ ሰዎች የመኖሪያ መንደራቸውንና የእርሻ ቦታቸውን ለይተው ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ኾኖም፣ ቤተክርስቲያን የሚስሙትና ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ተግባሮችን የሚፈጽሙት ገዳሙ በተሰየመበት ቤተ ክርስቲያን ሊኾን ይችላል፡፡ በገዳሙ ክልል (ሰበካ) ሌሎች ምዕመናን የሚኖሩ ከኾነ አመራር የሚሰጥበት ኹኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ አንዳንድ ገዳማት ደግሞ፣ ለምሳሌ፣ ዋልድባ፣ ደብረ ሊባኖስ በገዳሞቹ ክልል ሌላ ሰው ስለማይኖር የአበምኔቱ ኃላፊነት መነኰሳቱን ብቻ ማስተዳደር ይኾናል፡፡

ሰው በሕይወተ ሥጋ በሚኖርበት ጊዜ ወደ ገዳም በመግባት አንደበቱን ለጸሎት፣ እጁን ለምጽዋት እንዲዘረጋ በቃለ ግጥሞች ይመከራል፡፡ ሰው ከሥጋዊ ሕይወት ርቆ፣ መንኖ በገዳም እንዲኖር ከሚሰብኩ ቃለ ግጥሞች መካከል በይኄይስ ወርቄ (1968፤ 214) የተመዘገበው የሚከተለው አንዱ ነው፡፡

---

[2] ቆሞስ የሚለው ስም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያ ከኤጲስ ቆጶስ በታች ያለ፣ ከቄስ በላይ፣ የኾነ የቤተ ክርስቲያ መንፈሳዊ አባት፣ የኤጲስ ቆጶስ መጋቢ አገልጋይ ተለአኪ (፲፱፻፶፩ ፤ ፬፻፴፰)፡፡

[3] ኤጲስ ቆጶስ የሚለው መጠሪያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከቆሞስ በላይ፣ ከጳጳስ በታች የኾነ መንፈሳዊ አባት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል (፲፱፻፺፫፤ ፫፻፵፱)፡፡

ከሰው ዘንጋዳ[4] ገብተህ፣

ለምን ብቅ ጥልቅ ትላለህ፤

አሻግሮ ያየህ ፈጀው ይላል፣

ቆርጦ መሄድ ይሻላል፡፡

ቆርጦማ ለቀመሰው፣

ያ ገዳም ጣም አለው፡፡

"ቆርጦ መኼድ ይሻላል" የሚለው ስንኝ ሰማዊ መልእክት የዘንጋዳ አገዳን ወይም እሸትን ቆርጦ የሚበላ ሰው ማሳው ውስጥ ለረጅም ጊዜ ከሚቆይ ይልቅ ለሙበላት የሚፈልገውን የዘንጋዳ አገዳ ወይም እሸት ቆርጦ ቶሎ ከዘንጋዳው ማሳ ቢወጣ መልካም ነው፤ ብዙ ጥፋት እንዳላደረሰ ይቆጠራልና የሚል ነው፡፡ ዘንጋዳ አገዳውና እሸቱ የሚበላ የአገዳ እኽል ነው፡፡ የዚኹ የእኽል ዓይነት አገዳው ለመበላት በሚደርስበት ጊዜ ሰው መካን መካኑን (ፍሬ ማፍራት የማይችለውን) እየመረጠ ቆርጦ ይበላል፡፡ አንዳንድ ሰው ግን፣ ለአገዳው በመሰሰት ፍሬ ለማፍራት የሚችለውን ወይም በማፍራት ላይ ያለውን ዘንጋዳ ቆርጦ አገዳውን ሊበላ ይችላል፡፡ ፍሬ ለማፍራት የማይችለውን የዘንጋዳ አገዳ ብቻ እየመረጠ ቆርጦ የሚበላውም ቢኾን በዘንጋዳው ማሳ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ከቆየ ለማፍራት የሚችለውን ዘንጋዳ በመቁረጥ ብዙ ጥፋት እንዳደረሰ ይገመታል፡፡ ከእሸቱ የሚበላም ሰው መጥኖ ቆርጦ ከማሳው ቶሎ መውጣቱ በአገዳው እኽል ላይ የበዛ ጥፋት አላደረሰም ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለኾነም፣ በማሳ ውስጥ በመግባት የዘንጋዳ አገዳን ወይም እሸትን እየቆረጠ የሚበላን ሰው ዳር ቆሞ የተመለከተ ወይም ድርጊቱን የሰማ ሰው የሚያስፈልገውን ወይም የተወሰነ አገዳ ወይም እሸት ቆርጦ ከማሳው እንዲወጣ በግጥሙ ይመከራል፡፡ ከውጭ ኾኖ ለሚመለከት ሰውም ሐሜተኛ ኾኖ መሰናከል ውስጥ እንዳይገባ ከዕይታ ውስጥ ጥፋ ብሎ እንደመናገርም ይኾናል፡፡ ግጥሙን ያሰማው ሰው እሰው ዘንጋዳ ገብተኽ ብቅ ጥልቅ እያልክ ስትታይ ለተመልካች ብዙ አገዳ ወይም እሸት የቆረጥክ፣ ለአገዳው ወይም ለእሸቱ ስትል በዘንጋዳው ሰብል ላይ ብዙ ጥፋት ያደረስክ መስለኽ ትታያለኽና ለሙበላት የምትፈልገውን አገዳ ወይም እሸት ቆርጠህ ቶሎ ከዘንጋዳው ማሳ ውጣ በማለት በግጥሙ ሰማዊ ትርጉም ምክሩን አስተላልፏል፡፡

[4] ገጣሚው ለማለት የፈለገው እንደ ጥንቅሽ አገዳው የሚበላ፣ እሸቱም ተጠብሶ ሲበላ የሚጣፍጥ፣ ለሰውነትም ኀይልና ብርታት የሚሰጥ የአገዳ እኽል ዓይነት ነው፡፡ በጎንደርና በወሎ አንዳንድ ቦታዎች ማሩቴ ዘንጋዳ ተብሎም ይጠራል፡፡

“ያ ገዳም ጣእም አለው” የሚለው ስንኝ ሰማዊ ፍቺ የዘንጋዳ አገዳ ሲበሉት ጥሩ ጣእም ያለው ጣፋጭ መኾኑን ይገልጻል፡፡ ይኸም የአገዳውን የጣፋጭነት ስሜት ይነግራል፡፡ የአገዳውን

ጣእም በመቅመስ ለማረጋገጥ እንዲሞከር ይመከራል፡፡ ስንኙ ወርቃዊ ፍች መልእክት፣ የዓለምን ኑሮ ንቆ ለሥጋ ፍላጎት ሳይኾን ለነፍስ ዋጋ ይገኝበታል በሚባል ገዳም መኖር ለሕይወተ ነፍስ ተስማሚ ነው የሚል ነው፡፡ ገዳም ደግሞ “መነኮሳት ከዓለማዊ ኑሮ ተገልለው፣ በሃይማኖታዊ ሥርዓትና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተክርስቲያን ያለበት ቦታ” (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫፣ ፩፻፯) ነው፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሥጋ ኑሮን በመናቅ ገዳም መግባት መልካም ዋጋ የሚገኝበት፣ ሰማያዊ ሕይወትን ለመውረስ የሚያስችል ሥራ ለመሥራት አመቺ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ሰው ዓለማዊ ኑሮን በመተው መንፈሳዊ ኑሮን ለመኖር ገዳም መግባቱ ፈቃደ ሥጋን መተው ነው፡፡ መንኖ ገዳም መግባትም ከኹለተኛ ሞት ለመዳን ያስችላል ተብሎ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቶያን ይታመናል፡፡

የዚኽ ዓይነቱን ሃይማኖታዊ ምክር በግጥም መልክ (በኅብር ቅኔ ዓይነት) አያዘጋጁ በሊቀ መኳሶች (አዝማሪዎች) አንደበት በጥዑም ዜማ አማካይነት ለምእመናን ጆሮ እንዲደርስ ሲያደርጉ የነበሩት ከመሠረቱ ወይም ከጅምሩ የሃይማኖት ሊቃውንት ነበሩ፡፡ እኒኽ ሊቃውንት ዓላማቸው የሃይማኖት ትምህርት በአግባቡ የማያገኙትን ምእመናን እያዋዙ ማስተማር በመኾኑ በቀላሉ ወደ ልቦና ሰርጾ በሚገባና ለወንጌል ትምህርት ማስተማሪያ አመቺ በኾነ መንገድ እንዲኽ ዓይነቱን ድርሰት ለስብከታቸው ማስተላለፊያ ይጠቀማሉ፡፡ የዚኽ ቅኔ ኃይለ ቃል ጠቅላችሁ ገዳም ግቡ ለማለት ሳይኾን የወዲያኛው ዓለም እንዳይረሳ ለማስታወስ ሲባል የሚነገር ነው፡፡

በቅኔው በተለይም “ቆርጦ መሄድ ይሻላል” በሚለው ስንኝ ኹለት ተመሳሳይ መልእክቶች ተላልፈዋል፡፡ አንደኛውና ወርቃዊ ፍች የዓለምን ኑሮ ንቆ መመነን ዓለማዊ ኑሮን ከማፍቀርና በዓለማዊ ኑሮ ከመወሰን ይልቅ ወስኖ ጨክኖ ገዳም መግባት የተሻለ መኾኑን ይሰብካል፡፡ ምዕመናን ሕይወተ ሥጋን ንቀው እንዲተው መልእክቱ ይሰብካል፡፡ ኹለተኛው የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍቺ አንድን መልካም ነገር ለመፈጸም ከታሰበ ለዓላማው ኀያልና ቆራጥ መኾን እንደሚጠቅም ይመከራል፡፡ ውጤቱም ጠቃሚ ነው ይላል (አምኖ መሥራትን፣ የእምነት ሥራ ፍሬያማ መኾኑን ይሰብካል፡፡) (ቃለ መጠይቅ፣ መላኩ አዘነ፣ አዲስ አበባ፣ ፳፻፩)፡፡

ገዳም መግባትን ከሚሰብኩ ቃለ ግጥሞች መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡

ቤቱን በሸንበቆ የሚሰራ ማን ነው፣
ላወቀውማ ያ ገዳም መልካም ነው፡፡

ይኽ በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፻፵፪) የተመዘገበው ቃለ ግጥም በሰሙ ሸንበቆ በባህላዊው የቤት አሠራር ለቤት መሥሪያ ኾኖ ማገልገሉን ይገልጻል፡፡ አንደኛ፣ ተሰንጥቆ ጠሪያ ማገር ይኾናል፡፡ ኹለተኛ፣ ሳይሰነጠቅ ከወራጅ እንጨት ጎን በመሻጥ ከላይ የሣር ክዳኑን ይሸከማል፡፡ ከውስጥ በኩል ሲመለከቱት የተሻጠው ሸንበቆ ዐንጓው ወለል ብሎ ሲታይ ዐይንን ይማርካል፡፡ በሸንበቆ እንደ ተሰራ ቤት ባይኾንም ላወቀበት፣ ለተረዳውና ለተገነዘበው በዘንጋዳ ፣ በማሻላ የአዝርእት እኽል ዓይነነቶች አገዳ/ግንድ ቤትን መሥራት አይከፋም፣ መልካም ነው ማለትን ቃለ ግጥም በሠሙ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ቃለ ግጥሙ በወርቁ የገለጸው የገዳም ኑሮን ጥሩነት፣ ንዝንዝ ፣ ጭቅጭቅ የሌለበት፣ ለነፍስ የሚበጅ፣ ለሥጋ መውጣት መውረድ፣ ከሰውም ከራስም ጋር መጋጨት የሌለበት ሕይወት መኖር የሚቻለው በገዳም መኾኑን ይሰብካል፤ ይቀሰቅሳል፡፡

ዐለምን ንቆ፣ በጽሙና፣ በብሕትውና ለመኖር፣ ሥጋዊ ሕይወት እንደማይጠቅም ተረድቶ፣ ገንዘብን፣ ቤትን ትቶ በገዳም ለመኖር መመነን የሥጋዊ ሕይወት ምርጫ ሊኾን እንደሚገባ በቃለ ግጥሞች ይሰበካል፡፡ ይኽንን ከሚሰብኩት መካከል በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፻፵፫) የተመዘገበው የሚከተለው ቃለ ግጥም ያስረዳል፡፡

የኔም እኅት አንቺ፣ ያንቺም ወንድም እኔ፣

ምን መጠቅለያ አለው፣ ይኽ ዓለምናኔ፡፡

የግጥሙ ሠም እኔና አንቺ አንድ አካል ነን፤ ለኔም ላንቺም ሌላ ወገን ወይም አካል የለንምና ሌላ መመኘት የለብንም፤ ሌላውን እንደመናኝ ንቀን በቆራጥነት፣ በአንድነት ይኽን ዓለም እንጨርሰው፤ እንጠቅልለው፡፡ ወርቁ ደግሞ ከዚኽ ዘልዛላ ዓለም ለመላቀቅ የሚሻለው መመነን ነውና ኹለታችንም እንመንን፣ አንቺም እኔም ሌላ የምንፈልገው የለምና እኔ ካንቺ፣ አንቺ ከኔ ሌላ፡፡

ግጥሙን ያሰማው ሰው ያስጨነቀው የሱና የዓለም ነገር ፍጻሜ ነው፡፡ ስለኾነም " የዚኽ ዓለምና የኔ ነገር ፍጻሜው ምን ይኾን? ወየው መጨረሻችንን ላየው ሰው" በሚል ጭንቀቱን ገልጹዋል፡፡

በግጥሙ ወርቃዊ ፍቺ የተላለፈው መልእክት ግን "ይኽን ዓለም ጥሎ ከመኼድና መንኖ ገዳም ከመግባት በቀር የሚበጅ የለም፣ ቢለፉ፣ ቢወጡ፣ ቢወርዱ አይሞላም" የሚል ነው፡፡ ስለሆነም በግጥሙ ወርቃዊ ፍቺ እንደተላለፈው አንድ ሰው "የዓለምን ነገር ተድላና ደስታን ንቆና ትቶ፤ ከሰው ተለይቶ በዱር፣ በጫካ ወይም በገዳም" (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫፤ ፶፫-፶፪) ለመኖር መንኖ መኼዱ የተሻለ አማራጭ ተደርጎ መቆጠሩን ግጥሙ ያስረዳል፡፡ መመነን ደግሞ "ዓለምን መናቅና መተው፤ ከዓለም መሸሸ" ነው፡፡ ስለኾነም፣ አንድ ሰው መነነ ስንል "ዓለምንና በውስጡ ያለውን ኹሉ ናቀ፣ ተወ፣ አገር ጥሎ፣ ቁርበት ጠቅሎ፣

ጨልጦ፣ ገርኝቶ ኼደ፣ ታጣ፣ በርሓ ገባ፣ ከሰው ተለየ፣ በበአት (ዋሻ) ተከተተ፣ ለነፍሱ አደረ፣ ጤዛ ላሰ፣ ደንጊያ ተንተራሰ፣ በባሕር ላይ ቆመ፣ ኰሶ ቆረጠመ" (ደስታ ተክለውልድ፣ ፲፱፻፷፪፤ ፳፻፺፬) ማለት ነው፡፡ ስለኾነም፣ አንድ ሰው ዓለምን ንቆ ወደ ገዳም በሚገባበት ጊዜ መንፈሳዊ ተግባርን ለመፈጸም የሚያስችለው ምቹ ኹኔታ ይፈጠርለታል ተብሎ ይታመናል፤ ይቆጠራል፡፡

የሕይወተ *ሥጋን* ምቾት፣ ድሎት ወይም ለነፍሰ *ሥጋ* የሚደረገውን ውጣ ውረድ መናቅና ለሕይወተ ነፍስ መትጋት አስፈላጊ መኾኑ በቃለ ግጥም የሚሰበከው ሰው ዘላለማዊ

ሳይኾን፣ ዘመን የሚወስነው፣ ዕድሜ የሚገታው፣ *ሥጋ* ሞት የማይቀርለት መኾኑን በማሰብ ነው፡ ፡ ለሰው ሞተ *ሥጋ* የማይቀርለት፣ ታሥሮ፣ ተገንዞ ባፈር ውስጥ መውደቅ ዕጣ ፈንታው መኾኑን የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞችን ከዚኽ በታች በሚቀርበው ንዑስ እንመለከታለን፡፡

## ፫) የሞተ *ሥጋን* አይቀሬነት የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞች

የሰው ልጅ ፈቃደ *ሥጋውን* ለጥቂት ዓመታት እየፈጸመ ከኖረ በኋላ፣ ሞተ *ሥጋ* እንደማይቀርለት በዐማርኛ ቃለ ግጥሞች ይገለጻል፡፡ ሞት ዘገየም ፈጠነ የኹሉም ሰው ዕጣ ፈንታ መኾኑ የሰውን ልጅ ከንቱነት ያስረዳል፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሞት በኹለት ይከፈላል፡፡ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የነፍስ ከ*ሥጋ* መለየት ወይም የ*ሥጋ* ከነፍስ መለየት የመጀመሪያ ሞት ነው፡፡ ይኸም ሞተ *ሥጋ* ይባላል፡፡ ይኸ ዓይነቱ ሞት *ሥጋ* ለለበሰ ኹሉ የማይቀር፣ ሰው መልካም ምግባር በመ*ሥራት* አያልፈውም፡፡ በየትኛውም የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሰው *ሥጋ* ለባሽ በመኾኑ ከሞተ *ሥጋ* አያመልጥም፡፡ የመጀመሪያ ሞትም እንደ ማንቀላፋትም ይቆጠራል፡፡ ኹለተኛው ሞት፣ ሞተ ነፍስ ነው፡፡ ይኸም ሰው በሕይወተ *ሥጋ* በሚኖርበት ጊዜ መልካም ምግባር ባለመ*ሥራቱ*፣ ሕግን ባለማክበሩ፣ ከ*ሥጋ* ሞት በኋላ ነፍሱ ከእግዚአብሔር በመራቅ ለዘለዓለም በማይለወጥ ቅጣት ትወድቃለች፡፡ ከእንዲህ ዓይነቱ ሞትም መልካም ምግባር በመ*ሥራት* መዳን ይቻላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ምግባር ያልሠሩ ግን ነፍሳቸው መንጸፈ ደይን ትወድቃለች፣ ትኰነናለች፡፡ ሞት ብቻ ሳይኾን ሌሎችም የሚችሉ የሕይወት ተውሳኰች ሊኖሩና ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ "ምንም የለብኝ" ብሎ መዘናጋት አይበጅም፤ ሞትስ የታወቀ ነው፤ ንብረት፣ *ሥ*ልጣን፣ ጉልበት የማይመልሰው ያልታወቀ ክፉ ነገር ቢመጣስ? ብሎ ማሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ ከሞት *ጋ*ር ሊመሳሰሉ የሚችሉ አሉና ልክ እንደ ሞት ሊታዩ፣ ሊፈሩ ይገባል የሚል አመለካከት በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ሰፍኖ ይታያል፡፡

የሰው ልጅ ከሞተ *ሥጋ* እንደማያመልጥ የሚያስገነዝቡ ቃለ ግጥሞች በርካታ ናቸው፡፡ ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ በቅድሚያ በማኅተመ *ሥ*ላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩ ፤ ፴) የተመዘገበውን እንመረምራለን፡፡

መልካሙ አገር ጎንደር፣

ቤተክሲያን ስሞ ለመኖር፤

አይቀርምና መዳኘት፣

ከተማ ሰው መግባት፡፡

ቃለ ግጥሙ የሀዘንና የእንጉርጉሮ ስሜት የተገለጸበት፣ መዲና በመባል የሚታወቅና በመሰንቆ ወይም በበገና የሚዜም ነው፡፡ ሰማዊ መልዕክቱን ለማስተላለፍ የተቻለው፣ የጎንደር ከተማ የፍትሕና የዳኝነት ማዕከልና የሕዝብ መናሐሪያ ኾኖ ማገልገሉን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የቃለ ግጥሙ በሰማዊ ትርጉምም በገጠር የሚኖረው ሕዝብ ዳኝነትና ፍትሕ ለማግኘት በመፈለግ፣ ለሕግ ለመገዛት፣ ለመታዘዝ፣ የዳኛን ብያኔ ለመቀበልና ሥርዓት ለመያዝ ወደ ከተማ መግባቱ ግድ እንደኾነ ይገልጻል፡፡ የሰው ልጅ በሕይወተ ሥጋ ሲኖር ወደ ከተማ በመግባት የዳኛን ውሳኔ መቀበሉ ግድ ነው ተብሎ እንደሚታመነው ኹሉ፣ በሞት ዳኝነት ሞተ ሥጋን መቀበሉ፣ ከተማሰ፣ ከተቆፈረ መቃብር መግባቱ ምንም ቢኾን የማይቀር እውነታ እንደኾነ የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍች ያስረዳል፡፡ ሞተ ሥጋ ለሰው ልጅ የማይቀር ዕጣ ፈንታ እንደኾነ መንገርና ማስገንዘብ ዓለማዊ ሕይወት እንዲናቅና ዝቅ ተደርጎ እንዲታይ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡

ኹሉም የሰው ልጅ ሟች፣ አላፊ መኾኑን ከሚገልጹት ቃለ ግጥሞች መካከል የሚከተለውን በማኅተመ ሥላሴ መልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፸፫-፸፬) ሥራ ውስጥ የተመዘገበውን እንመለከታለን፡፡

የልጃ ገረድ አውታታ፣

አውራ መንገድ ላይ ተኝታ፤

ተነሽ በሏት ምነው፣

ይህ ሁሉ ዓለማፈር ነው፡፡

ይኽ ቃለ ግጥም በሰማዊ ፍችው ሀፍረት የማይሰማት ሥራ ፈትና ዘዋሪ የኾነች ልጃገረድ መተኛት በማይገባት ሰፈ መንገድ ላይ ተኝታለች፡፡ አሳፋሪ ድርጊቷን ተገንዝባ ማረም ካልቻለች እናንተ ከአስነዋሪ ወይም ከአዋራጅ ድርጊቷን እንድታርም ምከሯት፤ ተቆጧት፡፡

ዐይናውጣነቷን፣ ድርቅናዋን እንድትተው ግለጹላት፡፡ ብዙ ሕዝብና እንስሳ በሚኼድበት መንገድ ላይ መተኛቷ ነውር መኾኑን ነግራችኹ አስነሷት ማለትን ይገልጻል፡፡[5]

ይኽ ጽሑፍ ትኩረት ላደረገበት ደጋፊ የኾነው ሐሳብ የተገለጸው በቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍቾች ነው፡፡ ይኸውም ሰው ኹሉ፣ የአዳምና የሔዋን ዘር በሙሉ፣ ሟች ነው፤ ግብዓተ መሬት ይገባል፤ ይቀበራል ዐፈር ይበላዋል፤ ዐፈርም ይኾናል ማለት ነው፡፡ ቃለ ግጥሙ የሰው ልጅ ሟች መኾኑን ከመንገሩና ከማሳሰቡ በላይ ሰው በዓለም ላይ ሲኖር የሚጓጓላቸው አዱኛ፣ ተድላ፣ ደስታ፣ ሹመት፣ ሀብት፣ ንብረት፣ ጌትነት፣ ቅልጣን፣ ከንቱ መኾናቸውን ያዘክራል፡፡ እነዚኽን ነገሮች የሰው ልጅ በሕይወተ ሥጋ እያለ ቢያገኛቸው እንኳ ትቷቸው ያልፋል፡፡ የሰው ልጅ ኹሉንም ነገር ትቶ የሚያልፍ፣ የሚሞት ከኾነ፣ በሕይወተ ሥጋ ሲኖር ለተጠቀሱት ነገሮች ሊጓጓላቸው፣ ሊሻቸው፣ ሊመኛቸው አይገባም በማለት በቃለ ግጥሙ የተላለፈው መልእክት ይቀሰቅሳል፤ ይሰብካል፡፡

ሞተ ሥጋ ለሰው ልጅ ኹሉ የሚገጥመው የማይቀርለት ዕጣ ፈንታው መኾኑን እንዲያስብ ከሚቀሰቅሱት መካከል በማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፹፩፤ ፵፩) የተመዘገበው የሚከተለው ቃለ ግጥሞች ይጠቀሳል፡፡

በቅሎ[6] ከመንገድ ጠፍታኝ፣

ኰርቻ ይገኔ ስታዩኝ፤

እስቲ ኹላችኹም አስታውሱ፣

መርገፍ አለና እንዳትረሱ፡፡

ከበቅሎ ዕቃዎች አንዱን ኰረቻን ይገኔ የምታዩኝ፣ መንገድ ላይ በቅሎ ጠፍታኝ ነው፡፡ ከኰረቻው በተጨማሪ መርገፍ ተብሎ የሚጠራው የበቅሎ ዶቃ፣ ዘርፍ፣ አጫዋች ጌጥ ተረስቶ ወይም ተትቶ እንዳይቀርብኝ ኹላችኹም እንዳትዘነጉብኝ፣ እንዳትረሱብኝ የሚለው የቃለ ግጥሙ ሠማዊ ፍቺ ነው፡፡

---

[5]"ምስጢራዊው ፍች፤ ግራ የገባት ይህች ልጃገረድ መሄጃ አጥታ ሆድ ብሷት ባዳባባይ ተቀምጣለችና ከሐዘኗ አጽናኗት ምከሯትም (ተቆጣት) ዓለሙ ሁሉ አላፊ ቀሪ፤ ሰውም ሟች ከንቱ ነው ማለት የሆናል በማለት ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፹፩፤ ፲፰) ፍች ሰጥተዋል፡፡

[6]"በቅሎ አጋሰስ ካህያ ከፈረስ የሚደቀል፤ አባቱ አህያ እናቱ ፈረስ፡፡ ባላገሮች ከጥንት ከፍጥረት ስላልነበረ አህያና ፈረስን በማራከብ በሰው ዘዴ ስለ ተገኘ፤ በምድራችን እንዲኽ ያል በቅሎ አያውቅም ተባለ ይላሉ፤ የስሙም ምክንያት ይኽ እንደኾነ ይተርካሉ፡፡" አባቱ አህያ መባሉን መቀበል የማይፈልገው በቅሎ የአባቱን ማንነት ሲጠየቅ፡- በቅሎ አባትኽ ማነው ቢሉት እናቴ ፈረስ ነች አለ፡፡ በሌላ አባባል "በቅሎ አባትኽ ማነው ቢሉት ፈረስ አጎቴ ነው አለ፡፡" እየተባለ ይነገራል፡፡ (ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በአነስታይ ፆታም ይነገራሉ፡፡) የበቅሎ መልክ ግራጫ [ጠጉሩ/ሯ ነጭና ጥቁር የኾነ]፣ ዋርዳ [ጥቁር ጠጉር ያለው/ያላት በቅሎ]፣ ሽከላ [ቀይ በቅሎ]፣ ሳሙን [ፈገግ ያለ የበቅሎ መልክ]፣ ጨበር [ነጭ በቅሎ] በሚል ይታወቃል (ደስታ ተክለ ወልደ፣ ፲፱፻፷፩፤ ፻፹፫)፡፡ ጠጉሩ ጥቁረት ከቅላት የቀላቀለ ፈገግታ ያላው በቅሎ ዋርዳ ሳሙና ይባላል (ደስታ ተክለ ወልደ፣ ፲፱፻፷፩፤ ፩፻፹)፡፡ የበቅሎዎች መጠሪያ ስም ቀለማቸው ነው፡፡

የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍች የተላለፈው "መርገፍ አለና እንዳትረሱ" በሚለው ስንኝ ነው፡ ፡ መርገፍ የሚለው ቃል አውዳዊ ፍቺ መቅረትን፣ መለትን፣ መውደቅን፣ መንጠባጠብን፣ እመሬት ላይ ማረፍን፣ መፍረስን ይገልጻል፡፡ ዓለም ዐላፊ፣ መልክ ረጋፊ የሚለው ልማዳዊ አነጋገር አንድም፣ የሰው ልጅ የሚፈልጋቸው ደስታ፣ ተድላ፣ ሌላውም መልካም የሚባል ነገር ኹሉ ይቀራል፤ ማለትን ይገልጻል፡፡ አንድም፣ የሰው ልጅ መልኩ፣ ቁመናው፣ ሥጋው ይረግፋል፡፡ ከሞተ ሥጋ በኋላ፣ አስከሬን መቃብር ውስጥ ይገባል፤ ሥጋው ከአጥንቱ ተለያይቶ ይረግፋል፤ ሞት የሰው ልጅ ኹሉ ዕጣ ፈንታ መኾኑን ቀድመው የተገነዘቡት አልተገነዘቡም፣ አልተረዱም ላሏቸው መገኖች መምከሩን/መምከራቸውን እንረዳለን፡፡ መካሪው አንድ ሰውም ሊኾን እንደሚችል ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

ቀጥሎ በተጠቀሰው በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፵፫) በተመዘገበው ቃለ ግጥምም በሞት ከዚኽ ዓለም መለየታቸውን የተገነዘቡ፣ የተረዱ ሰዎች ለሌሎች ይነግራሉ፡፡

ብንጠይቃቸው የጥንቱን፣

ነዋሪ አይደለንም አሉን፡፡

በቃለ ግጥሙ የተነገረው ሰበካ የቀረበው በሠምና ወርቅ ነው፡፡ ጠያቂዎቹ ማወቅና መረዳት የፈለጉት የጥንቱን የነበረውን፣ ያለፈውን ታሪክ፣ ባህል፣ ወግ ነው፡፡ ተጠያቂዎቹ ደግሞ በቦታው ብዙ አለመቀየታቸውን፣ አለመኖራቸውን ፣ እንግዶች መኾናቸውን በመግለጽ የጥንቱን፣ ነበሩን ለጠያቂዎቹ ማስረዳት እንደማይችሉ ሠም ብለን በምጠራው የግጥሙ ፍች ገለጹ፡፡ ሞት የተናጋሪዎችና የሌሎችም ጨጣ ፈንታ መኾኑ የተነገረው በግጥሙ ወርቃዊ ፍች ነው፡፡ ይኸውም፣ "እኛም አንኖርም፤ አንሰነብትም፤ ሟቾች ነን፤ በዚህ ዓለም የመንቀር አይደለንም፡፡" የሚል ነው፡፡ የሚከተለው በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፵፫) የተመዘገበው ቃለ ግጥም ተመሳሳይ መልእክት የተላለፈበት ነው፡፡

ትላንት ተኝተው ሌሊት፣

አንቀዣበረኝ ያሉት፤

ሐሰትም አይደል እውነት፣

ይህ ሁሉ ያለሙት፡፡

ትላንት ሌሊት በተኙበት "አቃዡኝ"፣ "አንቀዣበረኝ" ያሉት ቅዠት አይደለም፡፡ ያዩት እውነተኛና ትክክለኛ ህልም ነው፡፡ አኹን ደርሶ፣ ተፈጽሞ የምናየው ኹሉ እርስዎ ያለሙት፣ በህልምዎ ያዩት ነው በማለት ቢቃለ ግጥሙ ሠማዊ ፍች ይገልጻል፡፡

የአዳም ዘር ኹሉ፣ ሟች መኾኑ የተነገረው በቃለ ግጥሙ የመጨረሻ ስንኝ "ይህ ሁሉ ያለሙት" በሚለው ነው፡፡ በአካል ገዝፎ ወይም ኰስሶ፤ በሀብት ጠልሞ ወይም በድኽነት ተቆራምዶ፤ በሥልጣን ከፍ ብሎ ወይም በምንዝርነት ዝቅ ብሎ የሚኖር ኹሉ፣ ሟች፣ አላፊ፣ ጠፊ መኾኑን ይገልጻል፡፡ ሥጋ ለባሽ፣ በሕይወተ ሥጋ እንዲኖር የተፈቀደለት ዘመን አለው፡፡ ከፈጣሪው የተፈቀደለት የዕድሜ ገደብ ሲደርስ ኹሉም ከሞት አይቀርም ማለትን ያስረዳል፡፡ ማሲንቆ ገራፊው አዝማሪ፣ በገና ደርዳሪው ዘማሪ በእንዲኽ ዓይነቱ ቃለ ግጥም የሚያስተላልፈውን መልእክት አድማጭ በተረጋጋና በተመስጦ በማዳመጥ ተመራምሮ እንዲረዳው ያደርጋል፡፡ የመልእክቱንም እውነትነት ይቀበላል፡፡ ለጊዜውም ቢኾን የሕይወተ ሥጋን ከንቱነት ያስባል፤ ያሰላስላል፤ ይተክዛል፡፡ እኽል እየበላ፣ ውሃ እየጠጣ ለመኖር መውጣት መውረድ በሕይወተ ሥጋ የሚፈጸም ግዴታውን ለማከናውን ሲታትር፣ የሕይወተ ነፍስን ጉዳይ በመዘንጋት፣ የሕይወተ ሥጋን ጉዳይ ያስቀድማል፡፡ ሰው ለሥጋ ሕይወቱ ቢወጣና ቢወርድ፣ ቢደክምና ቢታክት መጨረሻው ግባተ መሬት መኾኑን ከሚገልጹት ቃለ ግጥሞች መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡

ትልቅ አዳራሽ ሰርቼ፤
ሳንቃ ጉበኑን አበጅቼ፤

አፈሰሰብኝ ክዳኑ፤
ላፈርሰው ነው እዘኑ፡፡

ይኽ በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፵፯) የተመዘገበው ቃለ ግጥም ትልቅ ቤት ሰርቼ ከመቃን የሚወደደውን ባለ አራት ማዕዘን እንጨት ወይም ጉበንና ለበሩ መዝጊያ የሚኾነውን ሳንቃ ጠርቤ አዘጋጅቼ ገጠምኹ፡፡ ሳንቃው ተገቢውን አገልግሎት ይሰጥ ዘንድም በበሩ ግራና ቀኝ በመቆም ጉበኑን የሚደግፍ መቃን አዘጋጅቼ ገጠምኹ፡፡ የቤቱን ጣሪያ ሠራኹ፡፡ በአካባቢው የቤት ክዳን አሠራር መሠረትም፣ በሣር፣ በብር፣ በዐፈር ከደንኹ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጉድለት ስለ አለበት፣ ክዳኑ ዝናብን አይከላከልም፤ ያፈሳል፡፡ ክዳኑ በማፍሰሱም ምክንያት፣ ብዙ ደክሜ የሠራኹትን ሰፊ (ትልቅ) አዳራሽ ወይም ቤት ማፍረስ ግድ ኾነብኝ፡፡ አዳራሹን ቤቴን እንደማፈርሰው ስትሰሙ፣ እንደምታዝኑ" አምናለኹ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ክዳኑ በማፍሰሱ ምክንያት አዳራሼን ማፍረሴ፤ በደርጊቱም የእናንተ ማዘን አይቀሬ ነው፡፡ ይኽ የቃለ ግጥሙ ሠማዊ ፍቺ ነው፡፡

የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍችና የዚኽ ጽሑፍ ትኩረት የኾነው ሐሳብ የተላለፈው፣ “ላፈርሰው ነው እዘኑ” በሚለው ስንኝ ነው። በዚኽ ስንኝ ወርቃዊ ፍች የተላለፈው መልእክት ስለ ትልቅ አዳራሽ መሠራት፣ ሳንቃና ጉበን ስለ መበጀትና ክዳኑ በማፍሰሱ ምክንያት አዳራሹ ስለ መፍረሱ አይደለም። በስንኙ ወርቃዊ ፍች የተላለፈው መልእክት ሰው የተፈጠረው ለመሞት፣ ዐፈር ለመኾን ነው። ቃለ ግጥሙ “ዐፈር ነኽና ወደ ዐፈር ትመለሳለኽ” በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት፣ ማንኛውም ሰው ሟችና ፈራሽ በስባሽ ነው፤ ማለትን ይገልጻል። በቃለ ግጥሙ የተላለፈው መልእክት፣ ሞት ለኹላችኹም የማይቀር ዕጣ ፈንታ ነው። ሰው ሟች ፍጡር መኾኑን አውቃችኹ፣ እዘኑ፣ *ሥጋ* ለብሳችኹ፣ ምግብ በልታችኹ፣ ውሃ ጠጥታችኹ ስትኖሩ ሟችነታችኹን እንዳትዘነጉ በማለት ይሰብካል፤ ይቀሰቅሳል። በሟችነታችኹም፣ እዘኑ፤ የሞተን ሰው በእንባ የሚሸኙ ኹሉ፣ የሚያለቅሱት ለሟች ሳይኾን፣ ለራሳቸው ነው የሚለውን የባህሉን ባለቤቶች ግንዛቤ ይገልጻል።

የዛሬ ዘመን ገበሬ፣

መሬት አያውቅም እስከ ዛሬ፤

ጭንጫ ነው ብለህ አትተወው፣

ኧረ ሰው ዐፈር ነው።

የቃለ ግጥሙ ሠማዊ ፍች፣ የዘመኑ ገበሬ የሚያርሰው ጭንጫ ወይም ለም ዐፈር መኾኑን ለይቶ ዐያውቅም። በዚኽም ምክንያት፣ ሊታረስና እኽል ሊመረትበት የሚችለውን ለም ዐፈር ባለመረዳቱ ጭንጫ ነው ብሎ ሊተወው ወስኗል። ውሳኔው ስህተት ነው። የሚያርሰው መሬት ሊመረትበት የሚችል ለም ዐፈር ነውና ይረሰው የሚል ምክር የቀረበበት ነው።

የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍች፣ ሰው *ሥጋ* ለብሶ ቁሞ ሲታይ የማይሞት ይመስላል። ይሁን እንጂ፣ ሰው ሟች፣ በስባሽ፣ ፈራሽ፣ ዐፈር፣ ትቢያ፣ አቧራ የሚኾን ፍጡር ነው። የሰው መጨረሻው የሚያሳዝን ነው፣ የሚያስደምም ነው ማለትን ይገልጻል።

“ሰው ዐፈር ነው” የሚለው መልእክት በቃለ ግጥሞች በተለያዩ ቅርፆች ተደጋግመው ይቀርባል። የቅርፅ ለውጡን የሚከተለውን በማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፷፫-፷፬) የተመዘገበውን ቃለ ግጥም በአስረጅነት በመጥቀስ እንመልከት።

እዚያ ላይ ያለች ሸክላ ሠሪ፣

ድሃ ናት አሉ ጦም አዳሪ፣

ማን አስተማራት ጥበቡን፣

ገል ዐፈር መኾኑን፡፡

የቃለ ግጥሙን መልእክት ለማስተላለፍ ያገለገለው ሠሙ የሚገልጸው የተለያዩ የዐፈር ወይም የዐፈርና የአሸዋ ዓይነቶችን አዋህዳ ሸክላ የምትሠራ ሴት በኑሮ ያልተመቻት ድሃ ጦም አዳሪ መኾኗን ነው፡፡ ምንም እንኳ ድሃ ብትኾንም የምትሠራው ሥራ የሚደንቅ ነው፡፡ ለመኾኑ ሸክላ ከዐፈር የመሠራቱን ብልኀት፣ ጥበብ ማን ገለጠላት፤ ነገራት፤ ምን ሰው አስረዳት፣ እንዴት አወቀችው የሚል የመገረም፣ የመደነቅና ሸክላ የመሥራት ጥበቧ እፁብ ድንቅ ነው የሚል ሐሳብ ተገልጾበታል፣ በሠሙ፡፡

የቃለ ግጥሙ ዋና መልእክት የተነገረው በወርቁ ነው፡፡ ወርቁም፣ የሰው ልጅ ገላ፣ አካል ዐፈር፣ ትቢያ ነው የሚል ነው፡፡ ሰው ሚች፣ ዐፈር ቀማሽ፣ ተቀብሮ በስባሽ፣ በዐፈር ተለዋሽ፣ ወደ ዐፈርነት፣ ወደ መሬትነት ተለዋጭ፣ ትቢያ ኳኝ፣ መኾኑን በመግለጽ ለሥጋ ሕይወት ለመትጋት እንዳይጓጓ፣ ለሕይወተ ነፍሱ መሥራት ያለበትን እንዳይዘነጋ ይቀሰቅሳል፡፡

እስከ አኹን የተመለከትናቸው በመሰንቆ ወይም በበገና የሙዚቃ መሣሪያዎች በሚዜሙ መዲናና ዘለሰኛ ቃለ ግጥሞች ገዳም ስለ መግባት፣ ስለ ሕይወተ ሥጋ ሞት የተሰበከውን ነው፡፡ እንዲኽ ዓይነት ቃለ ግጥሞች የሚደረደሩት ወይም የሚዜሙት በአዝማሪ ወይም የኀዘንና የትካዜ ስሜት በተሰማው በገና ደርዳሪ ነው፡፡ በልመናና በለቅሶ ቃለ ግጥሞችም ተመሳሳይ መልእክት ይተላለፋል፡፡ በልመና አጋጣሚ ላይ የሚደረደሩት ቃለ ግጥሞች ሞት የሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ መኾኑን የሚገልጹ ቃለ ግጥሞች የሚደረደሩት ተለማኙ ምፅዋት እንዲሰጥ ፣ እንዲለግስ

ለማግባባት ነው፡፡ የለቅሶ ቃለ ግጥሞች ስለ ሞት እቀሬት መንገራቸው፣ መስበካቸው ቋሚ ለሟች ሳይኾን ለራሱ ያለቅሳል የሚባለውን ለማስረገጥ ነው፡፡ ከዚኽ በታች በልመና ግጥሞች ሞት አይቀሬነቱ እንዴት እንደተገለጸ እንመለከታን፡፡ በመጀመሪያ አባውዴዎች[7] ለልመና በሚደረድሯቸው ግጥሞች የሞትን አይቀሬነት የሚነግረውን ከዚኽ በታች የተጠቀሰውን እንመለከታለን፡፡

[7] በአባዉዴ የተደረደሩት ቃለ ግጥሞች በልመና አጋጣሚ ላይና በቃለ መጠይቅ ተሰበሰበው ለኹለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጥናት የቀረቡ ናቸው፡፡

ምን ጌታ ቢኾኑ፣ ባለዋርዳ በቅሎ፣ ባለማር እሸት፣

አሽከር ቢያደገድግ፣ ቀንና ሌሊት፣

ድጓ ቢተረጎም[8]፣ ቢነበብ ዳዊት፣

በቅሎ ቢያሰግሩት፣ ተጎንደር ይፋት፣

መቅረቱን አይቀርም፣ ከረምትና ሞት፡፡

ቃለ ግጥሙ በMesfin Messele (2000፡ 127) ጥናት የቀረበ ነው፡፡ ቃለ ግጥሙ የሰው ልጅ በዓለማዊ ኑሮው ምንም ያኽል በሀብት ቢጠልም፣ በዕውቀት ቢረቅ ጽዋ ሞት አይቀርለትም በማለት ይሰብካል፡፡ በማኅበረ ሰቡ ዘንድ ተመራጭ የኾነውን ዋርዳ በቅሎ ቢያሰግር፣ በጓሮው የማር እሸት ቢያመርት፣ ቀንና ሌሊት አሽከርም ኾነ ገረድ አደግድጎ ቢንከባከበው፣ ትልቁን የዜማ መጽሐፍ ድጓ ቢያዜምና[9]፣ ፻፶ መዝሙር ያለበትን ዳዊት (ጸሎት መጽሐፍ) ቢደግም፣ በገጠሩ ኅብረተ ሰብ ዘንድ የክብርና የጌትነት መግለጫ የኾነውን በቅሎ እያሰገረ ከጎንደር ይፋት መጓዝ ቢችል ከሞት እንደማያመልጥ በግጥሙ ተገልጹዋል፡፡ በመኾኑም፣ አንድ ሰው በግጥሙ የተዘረዘሩት ንብረቶች ኹሉም ወይም በከፊል ያሉት የተከበረና ጌታ የሚባል ሰው በሞት ይረታል፣ ይሸነፋል፡፡

በቃለ ግጥሙ ዓመት ጠብቆ የሚመጣው ክረምት (የዝናብ ወራት) እና የሰው ልጅ የሕይወት ፍጻሜ፣ ሕልፈት ተነጻጽረዋል፡፡ ኹለቱም ጊዜ ጠብቀው የሚመጡ፣ የሚፈጸሙ፣ ይቀራሉ ተብለው የማይታሰቡ ናቸው ተብሎ እንደሚታመን እንገነዘባለን፡፡

ከዚኽ በታች በተጠቀሰው ቃለ ግጥም የተላለፈው መልእክት ከላይ በተጠቀሰው ቃለ ግጥም ከተላለፈው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ምን ጌታ ቢኾኑ፣ የሞላው ንብረት፣

መጠራቱ አይቀርም፣ ከላይኛው ቤት፡፡

የተፈጥሮ ሥርዓት (ሕግ) ስለኾነም በኅብረተሰቡ ዘንድ በሹመት የደረጀ፣ በሀብት የበለጸገ ነው የሚባል ሰውም የመጨረሻ ጽዋ ሞት ነው የሚል መልእክት በግጥሙ ተላልፏል፡፡

[8] ድጓ ያሬድ የደረሳቸው ካመት እስካመት በሦስ ዓይነት ዜማ (ዕዝል፣ ዐራራይ፣ ግዕዝ) የሚጸለይ መንፈሳዊ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ የዜማ መጽሐፍ በመኾኑ ቢተረጎም ከማለት ይልቅ ቢጸነጸል/ቢንቆረቆር በሚል ቢተካ የተሻለ ነበር፡፡

[9]ከዓመት እስከ ዓመት በሦስት ዓይነት ዜማ (በዕዝል፣ በግእዝና በአራራይ) የሚጸለየውን ያሬድ የደረሰውን መንፈሳዊ ድርሰት ቢማርና ቢያዜም ለማለት ነው፡፡

ሰው በድህነቱ ምክንያት የሞት ጽዋን የሚቀበል፣ ሀብታምና የተከበረ በመኾኑ ከሞተ ሥጋ የሚያመልጥ ተደርጎ አይታሰብም፡፡ በዓለማዊ የኑሮ ደረጃቸው የሚበላለጡ ሰዎች ሞተ ሥጋ እኩል ያደርጋቸዋል፤ ኹሉም በሦስት ክንድ መሬት ይቀበራሉ፡፡ ሰው ድሃ በመኾኑ ሦስት ክንድ የመቀበሪያ መሬት አያጣም፡፡ ሀብታም በመኾኑም ከሦስት ክንድ የመቀበሪያ መሬት የበለጠ አይወስድም፡፡

ግጥሙ ሌላም መልእክት ያስተላልፋል፡፡ ሥርዓት ጠብቆ ተጠንቅቆ መኖር ለነፍስ ብቻ ሳይኾን ለሥጋ ሕይወትም ጠቃሚ መኾኑን ግጥሙ በግልባጩ ያስተላልፋል፤ ይሰብካል፡፡

በግጥሙ የመጨረሻ ስንኝ በሞተ ሥጋ ከዚህ ዓለም የተለየው ሰው ወደ ላይኛው ቤት፣ ወደ እግዚአብሔር ተጠራ ተብሎ ነው የተገለጸው፡፡ መጠራት ደግሞ መሞትን አያመለክትም፡፡ ይኸም ሞተ ሥጋ እንደ ማንቀላፋት ይቆጠራል የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያስታውሰናል፡፡ ያንቀላፋ ሰው ከእንቅልፉ እንደሚነቃው ኹሉ በሥጋ የሞተ ሰውም በትንሣኤ ቀን ይነሣል ተብሎ ይታመናል፡፡ የሰው ልጅ መጨረሻው ሞቶ መቀበር ስለመኾኑ ከሚደረደሩት ግጥሞች መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡

> ምነው ቀርቶ ቢኾን፣ የአዳም ልጅ ክብረቱ፣
>
> በስናር በበቅሎ፣ በፈረስ መምጣቱ፣
>
> የኋላ የኋላ፣ መሬት ሊኾን ቤቱ፡፡

የሰው ልጅ በዓለማዊ ኑሮው ተሳክቶለት በአካባቢው የክብር መግለጫ፣ የድሎት ምልክት ነው የሚባለውን በቅሎ ቢያሰግር፣ ፈረስ ቢጋልብ ዋጋ የሌለው መሆኑ በግጥሙ ተገልጹዋል፡፡ በግጥሙ እንደ ተገለጸው ሰው ሟች በመሆኑና መጨረሻውም ሞቶ መቀበር ስለኾነ ሀብት ማፍራቱና ትልቅ ሰው መባሉ ጥቅም የለውም፡፡ ዓለማዊ የኾነ ነገር ኹሉ በሞት ድል አድራጊነት ይቀራልና፡፡ ሰው ምነው ባልተፈጠረ፣ መጨረሻው አያምርምና የሚል ተስፋ አስቆራጭ ሐሳብ ሃይማኖታዊ ስብከት አይመስልም፡፡ ሃይማኖታዊ ስብከት የተስፋ ጭላንጭል ይነግራል ተብሎ ይታመናል፡፡

ሞት ሥጋ ለለበሰ ኹሉ አይቀርም የሚል መልእክት ከሚያስተላልፉ ቃለ ግጥሞች መካከል ደግሞ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

> ቅዱስ ሚካኤልን ፣ ገብርኤልን እመኑ፣
>
> ሞት አይቀርምና ምንም ቢመንኑ፡፡ (ጎሹ ሞገስ፤ ፲፱፻፷፬)

የዓለማዊ ኑሮን ንቆ "ከሰው ተለይቶ፣ እየፆመ፣ እየጸለየና እየሰገደ፣ በዱር በገደል ወይም በገዳም የሚኖር መነኩሴ መጨረሻም ሞት እንደኾነ ይኽ ግጥም ያስረዳል ፡፡

ከግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው "የዓለምን ነገር ተድላና ደስታ ንቆና ትቶ ከሰው ተለይቶ በዱር በጫካ ወይም በገዳም የሚኖር መነኩሴ ወይም መነኩሲት ሞተ ሥጋ የማይቀር ጽዋው ነው፡፡ ስሆነም "ከሰው ተለይቶ እየፆመ፤ እየጸለየና እየሰገደ፣ በዱር በገደል የሚኖር መናኝ፣ ናዝራዊ መነኩሴ" (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫፤ ፩፻፴፯) ቢኾን ይሞታል በማለት ሞት ሥጋ ለለበሰ ኹሉ የማይቀር መኾኑን ያስረዳል፡፡ ስለዚኽ እንዲህ ዓይነት ግጥሞችን በተለያዩ አጋጣሚዎች ማሰማት የሰው ልጅ ሞትን እያሰበ እንዲኖር በሕይወተ ሥጋ ትኩረት እንዳይሰጥ ተጽዕኖ ይፈጥራሉ፡፡ ሰው ሞተ ሥጋን እያሰበ ረጅም እቅድ በማቀድ ለሕይወተ ሥጋ ትኩረት እንዳይሰጥና ሞት መኖሩን እንዳረሳ እንዲያስታውስ ይቀሰቅሳሉ፡፡ በሌላ በኩል ግጥሙ እሙኑ የሚል ሐሳብ ብቻ የያዘ፣ ሌላ ለሥጋም ኾነ ለነፍስ የሚኾን ጠቃሚ ምክር የማይሰነዝር ነውና፡፡ እምነት ብቻውን ያለ ሥራ ፍሬ ቢስ መኾኑን ያላስተዋለ ነው፡፡

ምን ቢለባብሱ፣ ቢረቁ እንዳክርማ፣

መጠቅለል አይቀርም፣ በዘርዛራ ሰሌን በነጠላ ሸማ፡፡ (ኅሹ ሞገስ፤ ፲፱፻፷፩፤ 87)

በግጥሙ እንደ ተገለጸው በሕይወተ ሥጋ በሚኖሩበት ጊዜ ቢያጌጡ፣ ቢዋቡ፣ በመጨረሻ በገጠሩ እንደሚደረገው በሰሌን መጠቅለሉ፣ በነጠላ ሸማ መከፈኑ፣ በክር መታሰሩ አይቀርም፡፡ በግጥሙ ምን ማድረግ ይገባል፣ ይበጃል ለሚል ጥያቄ ጠቋሚና ጠቃሚ ሐሳብ አልሰነዘረም፡፡

አንድ ሰው ሲሞት ዘመድ ወዳጅ ተሰብስቦ ግጥም እየደረደሩ ማልቀስ በብዙ አካባቢዎች በተለይም በዐማራው ኅበረተ ሰብ ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ በለቅሶ አጋጣሚ ላይ ስለሟቹ ማንነትና ለቤተሰቡ ያኀደለውን ነገር እየቆጠሩ የለቅሶ ግጥም ይደረድራል፡፡ ከዚኽ ሌላ የሟቹን አስከሬን በዕንባ እየተራጩ የሚሸኙ እድምተኞችም የሞት ጽዋ ለእነሱም የማይቀርላቸው መኾኑን በለቅሶ ግጥሞች ይገልጻሉ፡፡ አጋጣሚውን በመጠቀም ቀደም ሲል የሞቱ ዘመዶቻቸውን ስም እየጠሩ ያለቅሳሉ፡፡ ቋሚዎቹም ሟች መኾናቸውን ለመግለጽ እንዲኽ በማለት ያለቅሳሉ፡፡

በሉ እናንተም ኺዱ፣ ነገም የኛ ነው፤

እግር እንኳ ሲኼድ፣ እየተርታ ነው፡፡

በሉ እናንተም ኺዱ፣ እኛም ወደዚያው ነው፣

ወትሮም መንገደኛ፣ ፊትና ኋላ ነው፡፡

ግጥሙ ቋሚው ሞት ያለበት መኾኑን እንዳይዘነጋ ከሞት አፋፍ የደረሰው፣ ለተረኞቹ (ለተከታይ ትውልድ) የሚያሰማ የማስጠንቀቂያ ደወል ነው፡፡ የእሱም ከንቱነቱንና ሰማያዊውን የጽድቅ ጉዳይ የሚሰብክ የጎላ መልእክት አይታይበትም፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሚሞቱት ቀድመው ለሞቱት ማልቀሳቸው ሙት ለሙት ያለቅሳል ይባላል፡፡ ይኸም፣ በሕይወት ያሉት የሞቱትን ሸኝተው (ቀብረው) የሚቀሩ ሳይኾኑ ውሎ አድሮ እነሱም ሟች መኾናቸውን ይገልጻል፡፡ የሃይማኖት መሪዎችም ኾኑ ትልልቅ ሰዎች በለቅሶው አጋጣሚ ላይ የሟች ቤተሰቦችና ሐዘንተኞች አምርረው ማልቀሳቸውን እንዲቀንሱ “የሞተው አይመለስም ማልቀሳችኹን ተው፡፡ ማልቀስስ ለራስ ነው” በማለት መምከራቸው ለዚኽ ነው፡፡ በዚኽም፣ የሞተው ሰው ወደ ማይቀርበት ዓለም መኼዱንና ኹሉም ሟች መኾኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚኽም በላይ ሰው ለሰማይ ቤቱ ሳይዘጋጅ ከሞተ ሲኦል ሊገባ፣ መንጸፈ ደይን ሊወድቅ ይችላል ማለታቸው ነው፡፡ ስለ ምድራዊ ሕይወት ብቻ ማሰብን ትቶ ከሞተ ሥጋ በኋላ ስለአለው ሕይወት እንዲያዘጋጅ መቀስቀሳቸው ነው ፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ “አምላክ እኔ ብቻ ነኝ፡፡ ከእኔ በቀር ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም፣ የምገድልም ሕይወትንም የምሰጥ እኔ ነኝ” (ዘዳግ. ፴፪፣ ፴፱) ተብሎ እንደ ተገለጸው ኹሉ ሞተ ሥጋን ፈጠረ የሚባለው እግዚአብሔር በግጥም ይወቀሳል፡፡

እኔ እግዜርን ብኾን፣ በጉልበቴ አልኰራም

ላላሰነብተው፣ ላፈርሰው አልሠራም፡፡

ይኽ በኀሹ ሞገስ (1964፤ 89) የተመዘገበው የልመና ግጥም እግዜር ሠርቶ አፍራሽ በመኾኑ ሰው መጫወቻው ኾኗል፡፡ ይኸን ድርጊት እኔ እንኳ አላደርገውም፤ አግባብ አይደለምና በማለት እግዜርን የሚተች እንጂ ከንቱነትን፣ ሰማያዊውን ዓለም የሚሰብክ አይደለም፡፡ ማጠቃለያ ነጥቡ የሰውን ከንቱነት የሚመለከት ነው፡፡

ሰው በሥጋ ሲሞት ነፍሱ ከሥጋው ከተለየ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል፣ ፍርዱንም ይቀበላል (መክ. ፲፪፣ ፪፡፡ ፪ቆሮ. ፭፣ ፩-፭፡፡ ፊልጵ. ፩፣ ፳፩ - ፳፫፡፡ ዕብ. ፱ - ፳፯፡፡ ያዕ. ፪፣ ፳፮)፡፡ “ከሞት በኋላ ትንሣኤ ስላለ ሞት ማንቀላፋት በሚል ቃል ተገልጧል” (፩ነገሥ. ፪፣ ፲፡፡ የሐዋ. ፯፣ ፳፱)፡፡ ሰው ሲሞት ነፍሱ አያንቀላፋም (ሉቃ. ፲፮፣ ፳፫ - ፳፬)፡፡ ፊልጵ. ፩፣ ፳፩ - ፳፮፡፡ ራእ. ፮፣ ፱ - ፲፩፤ ፳፣ ፬) (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ፲፱፻፸፪፣ ፶)፡፡ ስለኾነም፣ ከሞተ ሥጋ በኋላ ሰው ነፍሱ መንጸፈ ደይን እንዳይወድቅ በሕይወተ ሥጋ እያለ ከእሱ የሚጠበቀውን ሃይማኖታዊ ተግባር መፈጸም አለበት ተብሎ ይታመናል፡፡ በፍርድ ዕለት ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ፊት በእሳት ባሕር ላለመጣል በሕይወተ ሥጋ ሕግን መፈጸም፣ እንደ ሕግ መኖርና መመራት ይኖርበታል፡፡ ሰው እንደ ሕግ ከኖረ ከነፍስ ሞት ይደናል ማለት ነው፡፡

የሞትን ከባድነት ከሚገልጹት ቃለ ግጥሞች መካከል የሚከተለው በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፷፫) የተመዘገው ይጠቀሳል፡፡

ከጎዣምና ከዳሞት፣[10]

የቱ ይበልጣል በስፋት፤

እኔስ በግምት ባየው፣

ትልቁ ዳሞት ነው፡፡

በቃለ ግጥሙ አንድ ማንነቱ ያልተገለጸ ሰው ጎዣምና ዳሞት በመባል ከሚታወቁት ኹለት ግዛቶች የትኛው እንደሚሰፋ ይጠይቃል፡፡ ለጥያቄውም የራሱን ግምት መሠረት በማድረግ ሠፊው ግዛት ዳሞት የተባለው ነው በማለት ይመልሳል፡፡ ዳሞት የሚባለው ግዛት ወይም አገር ሠፊ ነው የሚለው የቃለ ግጥሙ ሠማዊ ፍች ነው፡፡

የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍቺ የተገለጸው "ትልቁ ዳሞት ነው" በሚለው ስንኝ ነው፡፡ ይኸም፣ አንድም፣ ከኹሉም የሚበልጠው ትልቁ የሰው ልጅ ዕዳ በሕይወተ ሥጋ ወይም በሕይወተ ነፍስ መሞት ነው፡፡ ሰውን ከሚያስጨንቁት የተለያዩ ችግሮች መካከል በሕይወተ ሥጋ አለመኖር ነው፡፡ አንድም፣ በሕይወተ ነፍስ ከመሞት የበለጠ የሚያስጨንቀው ከባድ ነገር የለም፡፡ የሕይወተ ነፍስ ሞት ዘላለማዊ ኩነኔን ያስከትላል ተብሎ መታመኑን ይገልጻል፡፡ ነገር ግን፣ የሕይወተ ነፍስ ሞት እንዳያጋጥም ሰው በሕይወተ ሥጋ እያለ የሚፈጽማቸው ተግባራት አሉ፡፡ ምጽዋት መስጠት፣ ሕግን ማክበር፣የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ቃለ ግጥሙ ሰው በሕወተ ሥጋ እያለ ከሞተ ነፍስ ለመዳን የሚጠበቅበትን ተግባር እንዲፈጽም ቃለ ግጥሙ ይመክራል፡፡

በቃለ ግጥሙ የተገለጸው እዳ የሚለው ቃል፣ አንድም፣ የሰው ልጅ ነፍሱን ከሥጋው እንዲለይ በማድረግ፣ ሞተ ሥጋን በመቀበል የሚከፍለው ቅጣት፣ ካሣ ነው፡፡ አንድም፣ ሰው ሐጢአት ወይም የሚያስኮንን ሥራ በመሥራት፣ ከሞት በኋላ ገሃነም በመግባት የሚደርስ የነፍስ ቅጣት ነው፡፡ ምንም እንኳ ሞተ ሥጋም፣ ሞተ ነፍስም የሰው ልጅ ትልቅ እዳዎች ቢኾኑም፣ የሚከተለው ቃለ ግጥም ትኩረት ግን ሞተ ነፍስ ላይ ነው፡፡

---

10 "...ታላቋ ጎጃም የተመሠረተችው በራስ ኀይሉ [ታላቁ] ጥበብና ጡንቻ...ነው፡፡ ከዘመነ ጎንደር እስከ ዘመነ ራስ ኃይሉ ጎጃም በመባል የሚታወቅ የዛሬው ምሥራቅ ጎጃም ብቻ ነበር፡፡ የዛሬው ምዕራብ ጎጃም ዳሞት፣ አገውና ሜጫ ተብሎ በሦስት የተለያየ ግዛት ነበር፡፡ ራስ ኃይሉ ራሳቸውን የቻሉና የተለያዩ ግዛቶች የነበሩትን የጎጃምንና የዳሞትን ደጃዝማችነት እንዲሁም፣ የይባባን አዛዥነት በመጠቅለል ለ32 ዓመታት ያህል ጎጃምን፣ ዳሞትንና አገውን ከመግዛቱ አልፎ ከእሱም በኋላ ከ1752 - 1924 ዓ. ም. ለተከታዮቹ ለ172 ዓመታት ውርስን ያመቻቸ መስፍን ነበር፡፡" (ሥርግው ገላው፣ 2002፤ 39)

ወደ ዳንግላ ሲኼዱ፣

ሩቅ ነው አሉ መንገዱ፤

ደምበጫ ስደርስ የመሸብኝ፣

ገና ዳሞት አለብኝ፡፡

ቃለ ግጥሙ በማኀተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፸) የተመዘገበ ሲኾን፣ ሠሙም "ወደ ዳንግላ በማደርገው ጉዞ ደምበጫ ስደርስ መሸብኝ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከአሰብኩት ቦታ ለመድረስ ገና የዳሞትን መንገድ መጓዝ አለብኝ፡፡" የሚል ነው፡፡

በወርቁ የተነገረው የቃለ ግጥሙ መልእክት ግን፣ የሰው ልጅ የሕይወተ ሥጋ ሞትን ሊከላከለው፣ ሊያስቀረው አለመቻሉና የማይቀርለት እዳ መኾኑ ነው፡፡ ይኽንንም ማኀተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል "እኔ" በሚል አንደኛ መደብ ተውላጠ ስም "ፍጡር ነኝ፣ ገና መሞት አለብኝ፤ የሞት ጽዋን እቀበላለሁ፤ "ወትገብእ ውስተ መሬት" ያለው ቃል ይፈጸምብኛል፡፡" በማለት ገልጸውታል፡፡ የሞት እዳ የአዳም ልጅ ኹሉ ነው ማለትን ያስረዳል፡፡

የሞት እዳ ወይም ኀልፈተ ሕይወት ለሰው ልጅ ኹሉ የማይቀር ዕጣ ፈንታ ስለ መኾኑ በማኀተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፵፪) የተመዘገበው የሚከተለው ቃለ ግጥም ያስረዳል፡፡

ማሳለፍማ እንደ ሞት ነው፣

አንድም ሰው አይቀረው፡፡

ይኽ ለሞት የሰው ባሕርይ በመስጠት የቀረበ ቃለ ግጥም ነው፡፡ ለሞት በተሰጠው የሰው ባሕርይም፣ በድግስ ላይ ለታደሙ ሳያዳላና ሳይዘነጋ ለኹሉም ሰዎች የሚበላና የሚጠጣ አንድ ባንድ በማስተናገድ፣ በማደል፣ በመስጠት በፈጸመው ተግባር የሚደነቅ የሚመሰገን መኾኑ በሠሙ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን፣ ማኀተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፵፪) እንደ ገለጹት በወርቁ የተላለፈው ዋናው መልእክት "ሞት የሚረሳው ሰው ከቶ አይገኝም፤ ይዋል ይደር እንጂ፣ ከሱ የሚቀር፣ ፈጽሞ የማይሞት፣ አንድም ፍጡር የለም" የሚል ነው፡፡ ለሞት የሰው ባሕርይ የሰጠው የሚከተለው ቃለ ግጥምም ሞት ያለ ማቋረጥ የሰውን ነፍስ ከመሬት ወደ ሰማይ ቤት እያመላለሰ መኾኑን ያስረዳል፤ ይነግራል፣ ያስተምራል፡፡

ሞት ፊደል ተምሮ ያነባል ስንል፣

እንኳን ሊያነብና ገና ያግዛል፡፡

ይኸ በማኅተ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፻፲፱) የተመዘገበው ቃለ ግጥም፣ ሞት ፊደልን በማየት፣ በመንካት፣ የፊደል ቆጠራ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት ግእዙን፣ ካዕቡን ለማወቅት እየተጣጣረ ማንበብ ይችላል ተብሎ መታሰቡን ሠሙ ይገልጻል፡፡ ሞት “ያለ ማቋረጥ ያዳምን ልጅ ወደ መቃብር ያግዛል” የሚለው ግን ቃለ ግጥሙ በወርቁ ያስተላለፈው መልእክት ነው፡፡

ሞት ያዳምን ልጅ ወደ መቃብር እንደሚያግዝ ሰው ይበልጥ የሚረዳው ሟችን በማሰብ ነው፡፡ የቅርብ ዘመድ ወይም ጓደኛ መሞቱ፣ መቃብር መግባቱ የራስን መጨረሻ ለማሰብ እንገደዳለን፡፡ የሚከተለው በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፫፻፸፯) የተመዘገበው ቃለ ግጥም ሰዎች ቀድመው የሞቱ ዘመዶቻቸውን በማሰብ ሟችነታቸውን በማሰብ የተከዙበት፣ ስለ ራሳቸው መጨረሻ ያወጡ ያወረዱበት ነው፡፡

ካልጋ መቀመጥ ከጠፍር፣

ይመስል ነበር የሚያምር፤

አባቶቻችን ብናያቸው፣

ሁሉም እመሬት ናቸው፡፡

በሠሙ እንደ ተነገረው፣ ከጠፍር በተሠራ ዐልጋ ወይም ወንበር መቀመጥ ደስ የሚልና ማኅበራዊ ክብርም የሚያሰጥ እንደኾነ ቢታወቅም ሽማግሎቹ አባቶቻችን ኹሉም የተቀመጡት እመሬት ላይ ነው፡፡ የቃለ ግጥሙ መልእክት የተገለጸው በወርቁ ነው፡፡ ይኸውም፣ አባቶቻችን ሞተዋል፤ መቃብር ገብተው መሬት ኾነዋል የሚለው ነው፡፡

ሞት የማይቀር የሰው ልጅ ዕዳ እንደኾነ ቢታወቅም፣ መቼ እንደሚመጣ የሚያውቅ ግን የለም፡፡ የሚከተለው በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፤ ፹፩) የተመዘገበው ቃለ ግጥም የሚነግረው ይኸንኑ ነው፡፡

ውሃ ሲሞላ አረምሞ፣

መጠበቅ ያሻል ከዳር ቆሞ፤

የሚያውቅ የለም ምን ቢሆን፣

የሚጠራበትን ቀን፡፡

በሠሙ እንደ ተገለጸው በእግር ይሻገሩት የነበረው ወንዝ ከአፍ እሰከ ገደፉ በድፍርስ ውሃ ተሞልቶ በፀታ ይጓዛል፡፡ በፀጥታ የመፍሰሱ ምክንያትም ውስጡን የሚያናጋው ድንጋይ ባለመኖሩ፣ በወጣ ገባ መሬት ሳይኾን፣ በሜዳ ላይ የሚገኝ ወንዝ በመኾኑ ነው፡፡ የሞላው ውሃ የሚጎልበትን፣ የደፈረሰው ውሃ ንጹሕ የሚኾንበትን ሰዓት፤ ጊዜ የሚያውቅ የለም፡፡

በወርቁ የተነገረው መልእክት ሥጋ ከነፍስ የሚለይበት፣ ሞት የሚመጣበት ጊዜ አይታወቅም የሚል ነው፡፡ መልእክቱ የተላለፈበት ጠራ የሚለው ግሥ በግጥሙ ባለው ዐውድ ሞት ጠሪ፣ ነፍስ ተጠሪ ናት፡፡ ጥሪውም ጊዜ የማይሰጥ በመኾኑ፣

የመጣ እንደኹ ሞት እንግዳ፣

ልዋል ልደር የለ ሥንቄን ላሰናዳ፡፡

በማለት ይገለጻል፡፡

"ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል" እንደሚባለው ሰው የሠራውን ሐጢአት አስታውሶ እግዚአብሔርን ይቅርታ ሳይጠይቅ፣ ምሕረት ሳይለምን ሞት ሳይታሰብ ድንገት ይመጣል የሚል ግንዛቤ አለ፡፡ ከክፉ ሥራ ወደ መልካም ሥራ መመለስ፣ በተሠራ ሐጢአት ተጸጽቶ በመጾም፣ በመጸለይ፣ መልካም ምግባር በመሥራት፣ አንደ ሕግ በመኖር፣ ሃይማኖት ሚያወግዘውን መጥፎ ተግባር ባለመፈጸም የእግዚአብሔርን ምሕረትና ይቅርታ መጠየቅ፣ ንስሐ መግባት ከሞተ ነፍስ ለመዳን ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከሞተ ነፍስ ስለ መዳን የሚደረደሩትን ቃለ ግጥሞች በሚከተለው ንዑስ ርእስ እንመለከታለን፡፡

### ፩) ከሞተ ነፍስ ስለ መዳን የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞች

ሞተ ነፍስ "የነፍስ ከእግዜር መራቅን፣ መንጸፈ ደይን መውደቅን" ያመለክታል፡፡ ምንም እንኳ ሰው "ከሰማይ ንጉሥ በእውነት በሚፈረድ ጥኑ ፍርድ የሥጋና[11] የነፍስ ቅጣት" (ራእ. ፲፰፣ ፲) ይደርስበታል ተብሎ ቢታመንም፣ ኩነኔን የነፍስ ቅጣት ብቻ አድርገ የሚቆጥሩ ቃለ ግጥሞች በርካታ ናቸው፡፡

የሰው ልጅ ከሥጋ ሞት በኋላ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ይወርስ ዘንድ በሕይወተ ሥጋ እያለ ለሕይወተ ነፍስ እንዲተጋ ቃለ ግጥሞቹ ይመክራሉ፡፡ ከሥጋ ሞት በኋላ ተንሣኤ ስላለ፣ ሰው በሥጋው ሲሞት ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለች፣ ፍርድንም ትቀበላለች ተብሎ ይታመናል፡፡ የሰው ልጅ ሞተ ነፍስ እንዳይሞት፣ ነፍሱ ከእግዚአብሔር እንዳትርቅ፣ መንጸፈ ደይን እንዳትወድቅ ሃይማኖታዊ ሕግን በማክበር፣ በእምነት በመኖር፣ ምጽዋት በመስጠት፣ ከኹተለኛ ሞት ይድናል ተብሎ ይታመናል፡፡

---

[11] የሥጋ ቅጣት፣ ሰው በሕይወተ ሥጋ እያለ የሚያጋጥመው የተለያየ ክፉ ነገር፣ ፍርጃ፣ የሥጋ ቅጣት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

*ሰው የሥጋ ግዴታውን ለመወጣት ሲታትር ሕይወተ ነፍሱን መዘንጋቱ ጸጸትን፣ ቁጭትን ያስከትላል፡፡ ይኽን ዓይነት ስሜት ከሚገልጹት ቃለ ግጥሞች መካከል በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፺፩፤ ፺፫) የተመዘገበው የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡*

*እወጥ ቤት ሄጄ ድንገት፣*

*ቋንጣ ጠብሼ ለመብላት፤*

*ወድቄ ነበር እሳት ላይ፣*

*ሥጋ ሥጋዬን ሳይ፡፡*

*ይኸ ግጥም በሠማዊ ትርጉሙ፣ ሥጋ ጠብሶ ለመብላት የፈለገ ሰው፣ ወደ ወጥ ቤት (ማድ ቤት) ይገባል፡፡ ጠብሶ ለመብላት በፈለገው ቋንጣ ላይ ትኩረቱን በማድረጉ፣ በወጥ ቤቱ (በማድ ቤቱ) ውስጥ ባለው እሳት ላይ ወድቆ ጉዳት ሊደርስበት እንደ ነበር ይገነዘባል፡፡ ከጉዳት መዳኑንም በእንኳን ተረፍኩ ስሜት ይግልጻል፡፡*

*ከዚኽ ጥናት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ትርጉም ሥጋዊ ኑሮዬ ላይ በማተኰሬ የነፍሴን ነገር ዘነጋኹ፡፡ ለሥጋዬ አድልቼ ኩነኔ ገባኹ፤ የሐጢአት ሥራዬ ከሞት በኋላ የስቃይና የፍዳ ቦታ ነው ለሚባለው ገሃነመ እሳት ዳረገኝ ማለትን ይገልጻል፡፡ የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍች ሰው በሕይወተ ሥጋ እያለ ከሞት በኋላ ኩነኔ እንዳይገባ የሥጋ ፍላጎቱን ብቻ እንዳያስብ፣ ለሕይወተ ነፍሱ እንዲያስብና እንዲተጋ ይመክራል፡፡ የሚከተለውን በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፺፩፤ ፵፯) የተመዘገበውን እንመልከት፡፡*

*ትንሽ አገልግል ሰፍተሽ፣*

*እንዳትጉላላ እባክሽ፤*

*እኛ እንኳ እንዳናያት፣*

*እዚያ ላይ ስቀያት፡፡*

*ቃለ ግጥሙ ስንደዶን ወይም አክርማን ሰበዝ በማድረግ በመርፌና በክር ወይም በወስፌና በግራምጣ ባለመክደኛ የስፌት ዕቃ (አገልግል) ሰፍተሻል፡፡ የሰፋሻት ትንሽ አገልግል እንዳትንገላታብሽ እኛ ከማናይበት ቦታ አርቀሽ፣ ደብቀሽ ስቀያት፤ አኑሪያት፤ አንጠልጥያት፤ የሚል ሠማዊ ፍች አለው፡፡*

"እዚያ ላይ ስቃያት" የሚለው የመጨረሻው ስንኝ የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍች የተላለፈበት ነው፡፡ እዚያ ላይ የሚለው ሐረግ ከፍተኛ ቦታን ይገልጻል፡፡ ከፍተኛው ቦታም በተለምዶ የሰማይ ቤት ተብሎ ይጠራል፡፡ የሰማይ ቤት ደግሞ፣ ከሥጋ ሞት በኋላ፣ ነፍስ የምትኼድበት ቦታ ነው፡፡ ቦታውም፣ ገነትና ገሃነም ተብለው የሚታወቁ ቦታዎች አሉበት፡፡ በሕይወተ ሥጋ መልካም የሠሩ፣ ሕግን ያከበሩ ጽድቅን፣ ገነትን ይወርሳሉ፡፡ ሐጢአት የሠሩ ለገሃነም ይዳረጋሉ፤ ኩነኔ ይገባሉ፡፡ ኩነኔውም በሰማይ ቤት ነው፡፡ ስቃያት የሚለው ቃል የመገልጸው፣ ከሞት በኋላ በሰማይ ቤት ጭንቅ፣ መከራ፣ ቅጣት፣ ኩነኔ፣ ገሃነመ እሳት አለ ማለትን ይገልጻል፡፡ ሰው ኩነኔ የሚገባው፣ በሕይወተ ሥጋ ሐጢአት በመሥራቱ፣ ሃይማኖታዊ ምግባር በማጉደሉ ነው፡፡ በሰማይ ቤት ሥቃይ ኩነኔ ገሃነመ እሳት አለ የሚለው የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍች የሰው ልጅ ለሕወተ ሥጋው በመትጋት ለገሃነም፣ ለኩነኔ እንዳይጋለጥ ቃለ ግጥሙ በተዘዋዋሪ መንገድ ይመክራል፡፡

የሰው ልጅ ለሕይወተ ሥጋው ቅድሚያ በመስጠቱ ለኩነኔ፣ ለገሃነመ እሳት እጋለጣለኹ ብሎ መሥጋቱን በቀጥታ ከሚገልጽባቸው ቃለ ግጥሞች መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡

ነፍሴ ያለውል ደንግጣ፣
ከግድግዳ ሥር ተሸጉጣ፤

አወጣትም ብል ቸገረኝ፣
ተሥጋ እንቢ አለችኝ፡፡

ይኸ በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፣ ፳) የተመዘገበው ቃለ ግጥም በሠሙ የተገለጸው ሰው በጋጠመው ወይም በሰማው ነገር እጅግ በመደንገጡ ነፍሱ ግድግዳ ላይ ተሸንቅራ ተጣብቃ መቅረቷ፤ ተቀርቅራ ተሰክታ ተወትፋ አልወጣም ማለቷ ነው፡፡ ነፍሱ ከደነገጠው ሰው ተለይታ ግድግዳ እንደ ተሻጠች ተደርጎ የተገለጸው ከተለምዷዊ አነጋገር በመነሣት ነው፡፡ ነፍስስ "ስጋ ለባሽ ለሆነ ፍጡር ሁሉ እንደ አንቀሳቃሽ ሞተር የምትቆጠር፣ ከፅንሰት እስከ እለተ ሞት ስጋን ተዋህዳ የምትቆይና በሞት ጊዜ ከስጋ የምትለይ ረቂቅ ህላዊ፣ ህይወት" ነች (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫፣ ፪፻፺፪)፡፡

በቃለ ግጥሙ ማስተላለፍ የተፈለገው ዋናው መልእክት ነፍሴ፣ ሕይወቴ "ከሥጋዊ ሥራ አልለይም አለች፤ ሥጋዊ ፈቃድ አየለባት፤ ዓለማዊ ሆነች" የሕይወተ ነፍስን ጉዳይ ዘነጋች፡፡

ለሕይወተ ሥጋ በማድላቷ፣ ለኩነኔ፣ ለገሃነመ እሳት ልትዳርገኝ ነው ሥጋት አደረብኝ የሚል ነው፡፡

የሚከተለው በማኅተመ ሥላለሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፣ ፹፫) የተመዘገበው ቃለ ግጥምም ለሥጋ ሕይወት በማድላት ምክንያት ነፍስ ለገሃነመ እሳት፣ ለኩነኔ መዳረጓን ይገልጻል፡፡

ይኽ ኹሉ ድግስ ተደግሶ፣

እንዳንሰደብ ዝግን አንሶ፤

ነፍሴ ለሥጋ አትሳሽ፣

ገና ፍሪዳ አለብሽ፡፡

ቃለ ግጥሙ በሠሙ ድግሱ ሰፊ፣ ብዙ ኾኖ እያለ፣ ዝግን፣ ምትር አንሶ ወጡ ውሃ የበዛበትና የቀጠነ ሥጋ ያነሰው እንዳይኾን፤ ያሰድባል፣ ያስተቻልና፡፡ ለሥጋ በመሰሰት መቆጠብ፣ ምትሩን፣ ዝግኑን ማሳነስ ተገቢ አይደለም፡፡ በቁጠባ የድግሱ ታዳሚ እንጋብዝ ወይም ሥጋ እናስተርፍ ብሎ ማሰብ ተገቢ አይደለም፡፡ የታረደው ፍሪዳ ሥጋ ቢይልቅ እንኳ ለእርድ የተዘጋጀ ፍሪዳ አለ፡፡ የተዘጋጀው ፍሪዳ ሲታረድ የበዛ ሥጋ ይኖራል፡፡ ከድግሱ ታዳሚ ሊተርፍም ይችላልና በሥጋት ለሥጋ መሰሰትና መቆጠብ ተገቢ አይደለም፡፡ ይኽ የቃለ ግጥም ሠም የሚገልጸው አንድ ሰው ለራሱ፣ ለነፍሱ የነገረውን፣ ሥጋቱን፣ ፍርሐቱን፣ በውስጡ ያወጣ ያወረደውን ነው፡፡

በቃለ ግጥሙ ማስተላለፍ የተፈለገው መልእክት በወርቁ የተነገረው ነው፡፡ ይኸውም "ፍሪዳ አለብሽ" በሚለው ሐረግ ወደ ፊት ነፍሴ "ሞት ኩነኔ ቅጣት አለብሽና ፍሪ፤ ለኋለኛው ዘመን አስቢ፤ ዕለተ ሞትን አስታውሺ፤ ዕዳ አለብሽ፡፡" በማለት የተነገረው ነው፡፡ ለኋለኛው ሕይወቱ አስቦና ተግቶ ነፍሱን ከሞት የዳነ ሰው ምስጉንና የታዳለ ነው ተብሎ ይቀናበታል፡፡ ይኽን ዓይነት ስሜት ከሚገልጹት ቃለ ግጥሞች መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡

የየሩሳሌም ነጋዴ፣

ጣለበት አሉ ወንበዴ፤

ለገንዘቡማ ማን አዘነ፣

ወየው ነፍሱን ያዳነ፡፡

ይኽ በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፷፩፣ ፸፫) የተመዘገበው ቃለ ግጥም በሠሙ ሸቀጥን እያጣራ ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየወሰደ በመነገድና በማትረፍ

የሚተዳደረው የየሩሳሌም ነጋዴ፣ ቀማኛ፣ ዘራፊ፣ ሽፍታ አደጋ ጣለበት፡፡ ገንዘቡን ዘረፈው፤ ቀማው፡፡ ገንዘቡስ ይቀማ፤ ይዘረፍ፣ ምን ይደረጋል፡፡ ሽቀጡ ገንዘቡ ቀርቶ ራሱን ነፍሱን ከሞት ያዳነ ከወንበዴ ያመለጠ ከወንበዴው ጥቃት በማምለጥ ነፍሱን ያዳነ፣ የታደገ ነጋዴ ምንኛ ብርቱ ነው፤ የሚል ፍች አለው፡፡

የቃለ ግጥሙ ወርቃዊ ፍች የተነገረው "ወየው ነፍሱን ያዳነ" በሚው ስንኝ ነው፡፡ "ወየው" የሚለው ቃል የሚገልጸው መጸጸትን፣ መቆጨትን ነው፡፡ ቁጭቱ ደግሞ ነፍስን ከሐጢአት፣ ከኩነኔ ለማዳን ባለመቻል ምክንያት የተፈጠረ ነው፡፡ እናም "ሰጥቶ መጽውቶ በበጎ ሥራውና በሃይማኖቱ ነፍሱን ከኩነኔና ከገሃነመ እሳት የሚያድን ሰው ምስጉን ነው፡፡" የሚለው የቃለ ግጥም መልእክት ነው፡፡

ስለኾነም፣ "ኩነኔ የማይለወጥ ለዘለዓለም በኃጢአተኞች ላይ የሚኾን የእግዚአብሔር ፍርድ ነው፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ በእምነት ያልተገኙ ይኰነናሉ (ዮሐ. ፫፣ ፲፰፡፡ ሮሜ. ፰፣ ፩)፡፡ ወንጌልን ዐውቀው የካዱ የባሰ ፍርድን ይቀበላሉ (ሉቃ. ፲፣ ፲፫-፲፭፣ ፲፪፣ ፵፯ - ፵፰)፡፡ "የኩነኔ ሁኔታ በጨለማና በእሳት ምሳሌነት ተገልጧል" (ማቴ. ፰፣ ፲፪፡፡ ማር. ፱፣ ፵፫ - ፵፰፡፡ ራዕ. ፳፣ ፲፭) (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ፲፱፻፸፪፣ ፻፺፯) ጨለማ "የኩነኔ" ኹኔታን ሲያመለክት (ማቴ. ፳፪፣ ፲፫፣ እሳት ደግሞ "የፈተና" (፩ጴጥ. ፩፣ ፮፣ ፯)፣ የፍርድ ምሳሌ ነው" (፩ቆሮ. ፫፣ ፲፪ - ፲፭)፡፡

ሰው በሕይወተ ሥጋ በሚኖርበት ጊዜ በእምነት መሠረት ካልኖረ፣ ወደ እግዚአብሔር ክብር ካልደረሰ (ሮሜ. ፫፣ ፲፩፣ ፲፪፣ ፳፫፣ ፲፬፣ ፳፫፡፡ ፩ዮሐ. ፫፣ ፬፡፡ ያዕ. ፪፣ ፲፣ ፬፣ ፲፯) ኃጢያተኛ ነው፡፡ ኃጢያት ብዙ ዓይነት ቢሆንም ዋናው ኃጢያት በእግዚአብሔር አለማመን ነው (መዝ. ፶፣ ፬፡፡ ሉቃ. ፲፭፣ ፲፰፡፡ ሮሜ. ፰፣ ፯)፡፡(የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ፲፱፻፸፪፣ ፻፹፫) "ኃጢያተኞች በፍርድ ዕለት ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ፊት በእሳት ባሕር ይጣላሉ፡፡ ይኸም ሁለተኛ ሞት ይባላል፡፡ ሥቃያቸውም አያልቅም (ኤር. ፳፣ ፲፩፡፡ ዳን. ፲፪፣ ፪ ማቴ. ፱፣ ፵፫፡፡ ፪ተሰ. ፩፣ ፱፡፡ ይሁዳ ፯፡፡ ራዕ. ፲፬፣ ፲፩፣ ፳፡፡ ፮፣ ፲፬) (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ፲፱፻፸፪፣ ፶)፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውን ፍርድ በተመለከተ በቃላዊ ግጥም እንደሚከተው ተገልጾ እናገኛለን፡፡

የሥጋ መከራ፣ ይፈጸማል በድሜ፣

የነፍሥ ፍዳ ነው፣ የሌለው ፍጻሜ፡፡ (ጎሹ ሞገስ፣ 1964፤ 106)

በግጥሙ የተነጻጸሩት የሥጋና የነፍስ ቅጣቶች ናቸው፡፡ ሰው በሕይወተ ሥጋ የሚቆይበት ጊዜ በእድሜ የተገደበ በመሆኑ የሥጋ መከራ ሰው በመሞቱ ምክንያት ይቀራል፡፡ ነገር ግን፣ ነፍስ የሚገጥማት ቅጣት ዘለዓለማዊና የማይለውጥ ነው፡፡ ነፍስ ዘለዓለማዊ በመኾንዋ ለጥፋት የተሰጠው ፍርድም ዘለዓለማዊ ነው፡፡ ነፍስን ከኩነኔ (ከፍዳ) ለማዳን ሃይማኖታዊ

ትእዛዛትን መፈጸም አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን ትእዛዛት ለመፈጸም መደረግ ያለባቸውና በተለይ በጎ ሥራ ላይ የሚያተኩሩት ተግባራት ፍቅርን፣ ምፅዋትን፣ መረዳዳትን... ወዘተ. የሚያካትቱ ስለኾነ ለምድራውያኑም የሚጠቅም ትምሕርት ነው፡፡

ሰው ከኩነኔ ለመዳን ምግባሩ የቀና፣ በእምነቱ የጸና የእግዚአብሔር ወገንና ለነፍሱ ያደረ መሆን አለበት ተብሎ ይታመናል፡፡ ሰው መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ፣ ሠማያዊ ክብርን ለማግኘት ሕግን መፈጸምና እንደ ሕግ መኖርንና መመራት ይኖርበታል፡፡ ስለኾነም ሰው ከሞተ ሥጋ በኋላ ጽድቅና ኩነኔ ያለ መኾኑን በመገንዘብ ከኩነኔ ለመራቅና በነፍስ በመጠቀም መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የሚያስችለውን ተግባር መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

ሰው ከሞተ ነፍሥ እንዲድን መፈጸም አለበት ከሚባሉት ምግባሮች መካከል አንዱና ዋነኛው ምፅዋት መስጠት ነው ፡፡ በፍትሐ ነገሥት (፲፱፻፷፪፤ ፻፵፫) ጌታችን "ምፅዋት ስጡ፣ ሁሉም ንጹህ ይሆንላችኋል" ማለቱ ተገልጹዋል፡፡ በተጨማሪም ጌታችን "ለለመነህ ስጠው" (ማቴ. ፳፭፣ ፴፬) ብሏል፡፡ "...ለሚራሩ ሰዎች ዓለም ሳይፈጠር ወደ ተዘጋጀላችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ግቡ ማለቱ፣ ሐዋርያው ጳውሎስም ለድሆች ምፅዋት መስጠትን አትዘንጉ ምሰሏቸዋም ማለቱ ሰው ይኸን በመሰለ መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል" (ዕብ. ፲፫፣ ፲፮) መባሉን በፍትሐ ነገሥት (፲፱፻፷፪፤ ፻፵፫) እናነባለን፡፡ ከዚኽም በላይ፣ "...ሰው ሁሉ ምጽዋት ከኃጢአት እንድታነጻ፣ በደልን እንድታስተሰርይ፣ ከክፉ እንድታድን ማመን ይገባዋል" (ፍትሐ ነገሥት፣ ፲፱፻፷፪፤ ፻፳፫)፡፡ ስለዚህ ፍጹም ሊኾን የወደደ ሰው ቢኖር ገንዘቡን ኹሉ መመፅወት ይገባዋል" (ፍትሐ ነገሥት፣ ፲፱፻፷፪፣ ፻፳፬) ተብሏል፡፡ ለተቸገሩ አዝኖ መስጠት፣ ድሆችን በልግስና መርዳት ታዝዞአል (ዘዳግ. ፲፭፣ ፲፩)፡፡ ሰው ሲመጸውት እግዚአብሔር ያያል፣ ይባርካልም" (ማቴ. ፮፣ ፩-፬)፡፡ "ምጽዋት በእግዚአብሔር መንግሥት ዋጋ እንዳለው ጌታችን አስተማረ" (ሉቃ. ፲፮፡ ፲፱)፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ለተቸገሩ አዝኖ መስጠት፣ ድሆችን በልግስና መርዳት ታዝዞአል (ዘዳግ. ፲፭፣ ፲፩)፡፡ ምጽዋት በእግዚአብሔር መንግሥት ዋጋ እንዳለው ጌታችን አስተማረ (ሉቃስ ፲፮፣ ፲፱)፡፡ (የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ፲፱፻፸፪፣ ፳፪)

በሌሎች መጻሕፍትም ምፅዋት በመስጠት ከኃጢአት መዳን እንደሚቻል ተገልጹዋል፡፡ በተአምረ ማርያም የሰውን ሥጋ በመብላት የሚታወቀው በላኤ ሰብእ የማርያምን ስም ጠርቶ ለለመነው ሰው ምፅዋት በመስጠቱ ጥፋቱ እነደተሰረየለት ተገለጹዋል፡፡ የሰው ሥጋ ይበላ የነበረው በላኤ ሰብእ የቅድስት ማርያምን ስም ጠርቶ ለለመነው ድሃ እፍኝ ውሃ መመፅወቱ ነፍሱ ወደ ሲኦል ከመውረድ እንደዳነች በሚከተለው ታሪክ ይነበባል፡፡

> ... ግብሩ በላኤ ሰብእ (ሰው በላ) በመባል የሚጠራ ስሞኦን የተባለ ሰው ነበር፡፡ በርኩስ መንፈስ አነሳሽነት ከልጆቹና ከሚስቱ ጋር 78 ሰዎችን በላ ይባላል፡፡ ስለዚህም በላኤ ሰብእ ተባለ፡፡ አንድ ቀን ውሃ በእርኮት ይዞ ሲሄድ የተመለከተው አንድ በሽተኛ "ስለ ቅድስት ማርያም" በማለት ውሃ እንዲያጠጣው ለመነው፡፡ በዚኽ ጊዜ በአእምሮ በነበረ ጊዜ ማርያም የሚለውን ስም ያውቅ ስለ ነበር ትዝ አለውና ከያዘው ውሃ በእጁ ላይ አፈሰሰለት፡፡ ከዚያ በኋላ በላኤ ሰብእ ክፉ

ሥራውን በመተውና ከሰው በመለየት ኖሮ ሞተ፡፡ ነፍሱ ወደ ሲኦል ልትወርድ ስትል ድንግል ማርያም በተሰጣት ቃል ኪዳን መሠረት ወደ ፈጣሪ ምልጃዋን አቀረበች፡፡ በጨረሻም የ78 ሰዎች ነፍሳትና እፍኙ ውሃ በሚዛን እንዲመዘኑ ተደረገና የነፍሳት ሚዛን ሊደፋ ሲል ቅድስት ማርያም በውሃው ሚዛን ላይ ጥላዋን ብትጥልበት እፍኙ ውሃ አመዘነና በላኤ ሰብእ ዳነ (ስንክሳር፣ የካቲት 16) (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፪፤ ፻፶፫)

ይኸም ኃጢአት የሠሩ ሰዎች የማርያምን ስም ጠርተው ለለመኑዋቸው ሰዎች ምፅዋት በመስጠት የዘለዓለም ሕይወት መውረስ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡ በላኤ ሰብእ የማርያምን ስም ጠርቶ ለለመነው ድሃ ባይመፀውት ኑሮ ነፍሱ ሲኦል በወረደች ነበር፡፡ ድንግል ማርያም በላኤ ሰብእን የማዳኗን ተአምር የሠሙ ምእመናን የእሷን ስም ጠርተው ምፅዋት እንዲሰጣቸው እንደሚከተለው ይለምናሉ፡፡

ስለማምላክ ብሎ፣ እጁን ያልዘረጋ፣

ሲገረፍ ይኖራል፣ በእሳት አለንጋ ፡፡

ስለ ምጽዋት በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረውን፣ በተአምረ ማርያም የሚነበበውን በፍትሐ ነገሥት የተባለውን ያነበቡና ያዳመጡ ምእመናን ምጽዋት መስጠት የሰማይ ቤትን ለመውረስ የሚያስችል መኾኑን እንዲቀበሉ፣ እንዲያምኑ ይገፋፋሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ምእመናን በተለያዩ አጋጣሚዎች የተሠበኩትን መነሻ በማድረግ ይመስላል ምጽዋት የመስጠትን አስፈላጊነት በተለያየ አጋጣሚ በግጥም ይገልጻሉ፡፡ በመኾኑም፣ ምጽዋት መስጠት የሰማይ ቤትን ለመውረስ የሚያስችል ስለመኾኑ የተለያዩ ግጥሞች ተደርድረዋል፡፡ እነዚኽንም ቀጥለን እንመለከታለን ፡፡

ዐይን ሲያይ፣ የሠጡት የመጸወቱት፣

ያስታርቃል፣ ከላይ ያገባል ገነት፡፡ (ኀሹ ሞገስ፣ 1964፤ 107)

ስለ ሰንበት ብለው፣ የመጸወቱት፣

አይከለከሉም፣ ሲገቡ ገነት፡፡

ከግጥሞቹ መረዳት እንደሚቻለው ሰው በሕይወተ ሥጋ በሚኖርበት ጊዜ ለተቸገሩ አዝኖ በልግሥና መርዳቱ ከዳግም ሞት ያድናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይኸም በመኾኑ፣ አንድ ሰው ምጽዋት በመስጠት እግዚአብሔር የወደደውን ነገር ከፈጸመ የዘለዓለም ሕይወትን ለመውረስ ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለኾነም፣ አንድ ሰው በዓለም ላይ በሕይወተ ሥጋ በሚኖርበት

ጊዜ ምጽዋት መስጠቱ ገነት ይገባል ተብሎ ይታመናል፡፡ ገነት ደግሞ፣ "ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በደስታና በፍቅር የሚገናኝበት ኹኔታ ነውና ጻድቃን ሲሞቱ የሚሄዱበት" (የመጽሐፍ ቅዱስ

መዝገበ ቃላት፣ ፲፱፻፸፪፣ ፪፻፵፪) ሰማያዊ ቦታ ነው፡፡ ገነት እግዚአብሔር ራሱ ያለበት እንደሆነ ክርስቶስ ተናግሯል (ሉቃ. ፳፫፣ ፵፫)፡፡ ገነት "ጻድቃን ወደ መንግሥት ሰማያት ከመግባታቸው በፊት ወይም እስከ ዕለት ምፅአት የሚቆዩበት ሰማያዊ ቦታ" ነው፡፡ (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫፤ ፫፻፫) ይኽንን የክርስትና ሃይማኖት እምነት መሠረት በማድረግም ምዕመናን የልመና ግጥሞችን ይደረድራሉ፡፡

ምጽዋት ሰጪው የሰንበትን ቀን በመጥራት በዚኹ ቀን ስም ሊመጸውት ይችላል፡፡ ሰንበት "የእግዚአብሔር ሥራ እንዲታወስ ያደርጋል፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለስድስት ቀን ሠርቶ እንዳረፈ ኹሉ ሰውም በዚኽ ዓለም ሠርቶ ወደ ዘለዓለም እረፍት እንደሚገባ ያመለክታል" (ዘፍጥ. ፪፣ ፪፣ ፫፡፡ ዘጸአ. ፳፣ ፰ - ፲)፡፡ (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ፲፱፻፸፪፣ ፸፩) (ሰንበት) "የጌታ ቀን" ነው (ሉቃ. ፷፩፣ ፷፩)፡፡ ስለኾነም፣ ሰንበት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን ኹሉ ፈጥሮ ያረፈበት ቀን ስለኾን ከሳምንቱ ቀናት ኹሉ የበለጠና የተቀደሰ ቀን ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ምጽዋት ፻፷፩) ጠያቂው የሰንበትን ቀን ጠርቶ አንድ ነገር እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ምጽዋት ሰጪውም የሰንበትን ቀን ጠርቶ በዕለተ ሰንበት ምጽዋት ሊሰጥ ይችላል፡፡ በመጨረሻዎቹ ኹለት ስንኞቸ እንደተገለጸው በሰንበት ስም የመጸወተ ሰው ገነት ለመግባት እንቅፋት አይገጥመውም ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለ ምፅዋት የተገጠሙት ግጥሞች የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምሕሮትን መሠረት ያደረጉ ያለው ለሌለው እንዲያካፍል እግረ መንገዳቸውን የሚያስተምሩ ናቸው፡፡

አንዳንድ ግጥሞች ከሞተ ሥጋ በኋላ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የሚቻልበት መንገድ ምጽዋት በመስጠት እንደኾነ ይሰብካሉ፡፡

ተዚያ ላይ ተዚያ ላይ፣ ተሥላሴ ደጂ ፣
በእግር አይደረስ፣ በእጅ እንድሆን እንጂ፣

የላይኛው መንገድ፣ በሩ አንድ ነው አሉ፣
መስጠት መከፈቻውን፣ ሳያውቀው ሰው ሁሉ፡፡

የላይኛው መንገድ፣ ቀጭን እንደመርፌ፣
በሰጠሁ ያሰኛል፣ ልብሴን ተገፍፌ፡፡

“ተዚያ ላይ” የሚለው ሐረግ የሚገልጸው ሰማይ ቤትን ነው፡፡ ሰማይ ቤት ደግሞ ከሞት በኋላ ነፍስ ትኼድበታለች ተብሎ የሚታመንበት ቦታ ነው፡፡ በክርስትና ሃይማኖት ሥላሴ የሚለው የእግዚአብሔር በአካል፣ በስም በግብር የሦስትነቱ መግለጫ ስም ነው፡፡ (የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ፲፱፻፺፫፤ ፻፯) “ሥላሴ የሚባሉ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በስም፣ በአካል በግብር ፫ ናቸው፡፡ በባሕርይ፣ በህልውና በመለኮት አንድ ናቸው፡፡” (ይኄይስ ወርቄ፣ 1968፤ 221) ግጥሙን ያሰማው ሰው ከሕልፈተ ሕይወት በኋላ ነፍስ መንግሥተ ሰማያትን መውረስ የሚቻለው በሕይወተ ሥጋ እያሉ ምጽዋት በመስጠት ነው ይላል። ነፍስ እግር ኖሯት ዘለዓለማዊ ሕይወት ወደሚገኝበት ወደ ሥላሴ ደጅ (መንግሥተ ሰማያት) አትኼድም አትችልም፡፡ ለዚህም ነው ገጣሚው መንግሥተ ሰማያት የሚደረሰው በእግር ሳይኾን በእጅ ነው የሚለው፡፡ ይኸም ምጽዋት በመስጠት፣ በጎ ምግባር በመሥራት የተቸገሩትን በመርዳት መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ይቻላል ለማለት ነው፡፡ ምጽዋት መስጠት የሚቻው ሰው በሕይወተ ሥጋ ባለበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ሰው ነፍሱ ከሥጋው ከተለየች በኋላ ምጽዋት በመስጠት መንግሥተ ሰማያትን መውረስ አይቻልም፡፡ በመኾኑም ነፍስ ወደ ሥላሴ ደጅ (መንግሥተ ሰማያት) መድረስ ትችል ዘንድ በሕይወተ ሥጋ እያለ ምጽዋት መስጠት እንዳለበት ግጥሙ ያሳስባል፡፡ በግጥሙ የተላለፈው መልእክት መረዳዳትን፣ ተካፍሎና ተሳስቦ መኖርን፣ በጎ ምግባር የሚሰብክ፣ ለሰማያዊው ብቻ ሳይኾን ለምድራዊው ኑሮም ጠቃሚ ትምህርት ነው፡፡

ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የሚቻለው በአንድ መንገድ ብቻ ነው፡፡ መንገዱም በእውነታው ዓለም እንደሚታወቀው በእግር ተጉዘው በአካል የሚኼዱበት ሳይኾን ለሌለው አዝኖ በመስጠት፣ በመለገሥና በመመጽወት በበጎ ምግባር የሚታለፍበት መንገድ ነው፡፡ ምጽዋት መስጠትም የመንገዱን መግቢያ በር መክፈቻ ቁልፍ ነው ተብሎ መታመኑን ገጣሚው ይጠቁማል፡፡ ስለዚኽ ሰው በሕይወተ ሥጋ እያለ ድኾችንና የሚለምኑትን ከመጸወተ ወደ መንግሥተ ሰማያት የመግቢያውን በር ሊከፍት የሚችል ቁልፍ እንደያዘ መታመኑን ግጥሙ ይገልጻል፡፡ በሌላ በኩል፣ ምጽዋት ካልሰጡ እግዚአብሔር የሚወደውን ምግባር አልፈጸመምና ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይችልም የሚል መልእክት ይነግራል፡፡ ምጽዋት በመስጠት ድሆችን አለመርዳት ግን ጸጸትንና ቁጭትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ለምጽዋት የሚሆን ገንዘብ ባይኖር እንኳ የለበሱትን ልብስ ከላያቸው አንስተው በሰጠሁ ያሰኛል፡፡ በቀጭኗ መንገድ ለማለፍ አለመቻል ደግሞ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት አለመቻል ነው፡፡ ይኸ ደግሞ የዘለዓለም ስቃይና መከራ ውስጥ መውደቅን፣ ገሃነመ እሳት መግባትን ይጠቁማል፡፡

ለልመና ወደ አንድ መንደር የኼደ ሰው የሰማዕታትን፣ የመላእክትን፣ የጻድቃንን፣ የኢየሱስን ወዘተ. ስም በመጥራት ይለምናል፡፡ ምጽዋት የሚሰጠው ሰውም ለማኙ የሰማዕታትን፣ የመላእክትን፣ የጻድቃንና የኢየሱስን ስም በመጥራቱ ቶሎ ብሎ እጁን ለምጽዋት ሊዘረጋ ይችላል፡፡ መጽዋቹም እነሱን ጠርቶ ይዘክራል ወይም ይመጸውታል፡፡ ለምሳሌ፣ ምጽዋት ጠያቂው የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ስም ጠርቶ ምጽዋት ይለምናል፡፡ ተለማኙም ስለ እመቤታችን ክብር ሲል የእሷን ስም በመጥራት ምጽዋት ይሰጣል፡፡

እመቤታችንን፣ አማላጅ አብጁ፣

በቅርብ አይገኝም፣ የሥላሴ ደጁ፡፡

እመቤቴ ማርያም፣ እመቤቴ ሆይ፣

ያንችን ስም የጠራ፣ አይማርም ወይ፡፡

ስለ ማርያም ብሎ ሲለምን የመጸወተ ሰውም በሕወይተ ሥጋ በነበረበት ጊዜ የሠራው ኃጢአት ይሻርለታል፣ ምሕረት ይደረግለታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይኸ እንደሚኾን በስንክሳር ላይ ስለ በላኤ ሰብእ የተገለጸውን ቀደም ሲል አንብበናል፡፡

**፮) የሀብተ ሥጋን ቀሪነት የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞች**

የሀብተ ሥጋን ቀሪነት የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞችን ከመመልከታችን በፊት የሀብተ ሥጋን ምንነት በአጭሩ መግለጽ አስፈላጊ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል (፲፱፻፺፫፤ ፴) ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት ሀብተ ሥጋ የሚለው ስም ምድራዊ ጸጋ፣ ሀብት ማለት ነው (ገጽ፣ ፴)፡፡ ፀጋ የሚለው ቃል ፍች "አምላካዊ ስጦታ፣ ሀብት፣ ረድኤት" ማለት ነው (ገጽ፣ ፫፻፹፩)፡፡ ሀብት ደግሞ አንድም ንብረት፣ ጥሪት ማለት ነው፡፡ አንድም፣ ዕድል፣ ዕጣ ማለት ነው (ገጽ፤ ፴)፡፡ ንብረት የሚለው ስም ፍች፣ የማይንቀሳቀስ (እንደ ቤት፣ ቦታ፣ ያለ ሀብት ጥሪት) እና የሚንቀሳቀስ ሀብት ማለትን ይገልጻል (ገጽ፣ ፪፻፺፫)፡፡ ሀብተ ሥጋ ሰው በሕይወተ ሥጋ ወይም በዓለመ ሥጋ የሚያገኘውን/ኛቸውን ወይም ያገኘውን/ኛቸውን መልካም ነገር/ነገሮች ኹሉ ያጠቃልላል፡፡ በዓለመ ሥጋ ተሳክቶለት፣ ተመችቶት፣ ደልቶትና ተደስቶ የሚኖር ሰው ዓለም ዐየ ይባላል፡፡ ዓለም የሚለው ቃል፣ "አዱኛ፣ ተድላ፣ ሹመት፣ ሀብት፣ ንብረት፣ ጌትነት፣ ሥልጣን" ማለትን ይገልጻል። እነዚኽ የዓለመ ሥጋ ሀብቶች አላፊ፣ ጠፊ፣ ቀሪ መኾናቸውን ለመግለጽ "ዓለም ዐላፊ፣ መልከ ረጋፊ፤ ዓለም ዘዋሪ፣ ዓለም ዋሾ፣ ዓለም አታላይ" በማለት ይነገራል (ደስታ ተክለ ወልድ፣ ፲፱፻፷፪፣ ፱፻፴)፡፡

ምእመናን በተለያዩ አጋጣሚዎች የተሰበኩትን ወይም የሰሙትን ሃይማኖታዊ ቃል መነሻ በማድረግ ለሥጋ የሚኾን ንብረት ከማጠራቀም ይልቅ ለነፍስ ዋጋ የሚኾን ምጽዋት መስጠት የተሻለ መኾኑን ይሰብካሉ፡፡ ከዚኽም በላይ፣ ሰዎች ለምድራዊ ዓለም ብለው የሚሠሩት ቤት፣ የሚያጠራቅሙት ሀብት፣ ሰው በሞተ ሥጋ ከዚኽ ዓለም በሚለይበት ጊዜ ቀሪ መኾናቸውን እዲያስቡ ይቀሰቅሳሉ፡፡ ለጊዜያዊውና ለምድራዊው ዓለም ምቾትና ድሎት ከማሰብና ከመጨነቅ ይልቅ ለዘለዓለማዊና ለሰማያዊ ቤት ማሰብና መጨነቅ እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡ ምጽዋት በመስጠት እግዚአብሔር የሚወደውን ሥራ እንዲሠሩ ይመክራሉ፡፡

ሰው በሕይወት ዘመኑ በዓለመ ሥጋ እያለ ያፈራው ንብረት በሕይወተ ሥጋ ሞት ቀሪ መኾኑን ቃለ ግጥሞች ይገልጻሉ፡፡ እነዚኽ ቃለ ግጥሞች፣ ሰው በሕይወተ ሥጋ ሲኖር ያፈራውን ንብረት አከማችቶ ከመያዝ ይልቅ፣ ለሕይወተ ነፍስ እንዲረዳው ምጽዋት የመስጠቱን ተገቢነት ይሰብካሉ፡፡

ስጥለት ቾርለት፣ አበድርለት፣

ቁጭ ብሎ ቀሪ ነው፣ ደበሎ ነው ቤት፡፡ (ጎሹ ሞገስ፣ 1964፤ 89)

በላይ ቤት ሥራ እንጂ፣ ጠለል ያለ አዳራሽ፣

ይኸማ የምድሩ፣ ቀሪ ነው ለወራሽ ፡፡ (ጎሹ ሞገስ፣ 1964፤ 92)

ቃለ ግጥሞቹ ሰው በሕይወተ ሥጋ ባለበት ጊዜ የሚሠራውና የሚያከማቸው ሀብትና ንብረት ዋጋ ቢስ መኾኑን የሰማይ ቤት ቢኾን ኖሮ ግን መፍረስ እንደማይችል ይገልጻሉ፡፡ ሰዎች በሕይወተ ሥጋ በሚኖሩበት ጊዜ የሚሠሩት ዓለማዊ ነገር ሁሉ ቀሪና ፈራሽ መኾኑን ይሰብካሉ፡፡ በሕይወተ ሥጋ በሚኖሩበት ጊዜ ሀብትና ንብረት ማጠራቀም፣ እንደዚሁም በሹመት ከፍተኛ ደረጃ መድረስ ቀሪና "እንዲህ ነበር" ከማለት በስተቀር የሚፈይደው ነገር አለመኖሩን ያስገነዝባሉ፡ ፡ ከፍተኛ ደረጃ ደርሿል የሚባል ማንም ሰው ሕይወቱ የሚቋጨው በሞት መሆኑንም ግጥሞቹ ይገልጻሉ፡፡ ይኸም፣ ሰዎች ለዓለማዊ ኑሮ ትኩረት እንዳይሰጡ ይሰብካል፡፡ እንዲህ ዓይነት ግጥሞችንም ተለማኞችን ለማግባባት ለማኞች ሲጠቀሙባቸው ይደመጣሉ፡፡

ሰው በምድር ላይ በሚኖርበት ጊዜ ሰፊ አዳራሽ ቢሠራና ከፍተኛ ንብረት ቢያጠራቅም በሚሞትበት ጊዜ የመውረስ መብት ለአለው ሰው ጥሎለት ይኼዳል፡፡ ይኸም ሰው በሕይወተ ሥጋ እያለ የሚያጠራቅመው ንብረት ዋጋ እንደሌለው ይጠቁማል፡፡ ሰው በምድራዊ ሕይወት ዘመኑ ሰፊ አዳራሽ ከመሥራትና ንብረት ከማከማቸት ይልቅ ለሰማይ ቤት መግቢያ የሚኾን በጎ ምግባር እንዲሠራ ይመከራል፡፡

ገጣሚው ሰፊ አዳራሽ የሚለው በመሬት ላይ እንደሚታወቀው ዓይነት ቤት ሥራ ሳይሆን በህይወተ ሥጋ እያለ የዘለዓለም ሕይወትን ለመውረስ የሚያስችል ምግባር እንዲሠራ ይመከራል፡፡ ይኸውም በመሬት ላይ እያለ በመለገስና በመመጽወት የሰማይ ቤቱን እንዲያዘጋጅ የሚመክር ነው፡፡ ይኸም ሰው በሕይወተ ሥጋ ባለበት ወቅት የሚሠራው ሰፊ አዳራሽ፣ የሚያጠራቅመው ንብረት፣ ለእሱ ጥቅም እንደሌለው ተረድቶ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ እንዲችል ከንብረቱ ቀንሶ መመጽወት ይገባል በማለት ይመከራል፡፡

ግድግዳው ቢረዝም፣ ምን ባጡ ቢያምር፣

የምድር ቤት ነውና፣ መፍረሱ አይቀርም፣

ይኸ በማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (፲፱፻፳፩፤ ፪፻፸፫) የተመዘገበው ቃለ ግጥም በሰሙ የገጠሩን የቤት አሠራር በተለይም ለተወሰነ አካባቢ ተስማሚ ነው የሚባልን የግድግዳ መርዘም ይገልጻል፡፡ አንድ ሰው የሠራው ቤት በአካባቢው ጥሩ ቢባልም ቋሚና የዘለዓለም አለመሆኑን ግጥሙ ይጠቁማል፡፡ ምክንያቱም የቤቱ መሠረት በዐፈር ላይ የቆመ በመኾኑ ሰው በሕይወተ ሥጋ በሚኖርበት ጊዜ ይስማማኛል እኖርበታለኹ ብሎ የሠራውን ቤት ውሎ አድሮ ጥሎት እንደሚኼድ ቃለ ግጥሙ ይጠቁማል፡፡ ስለኾነም፣ ሰው መሬት ላይ የሚሠራው ቤት የሚያከማቸው ሀብትና ንብረት ዋጋ ቢስ፣ ፈራሽ፣ ቀሪ መኾኑን ይገልጻል፡፡ ሰማያዊ ሀብት ወይም የሰማይ ቤት ቢኾን ኖሮ ግን መፍረስ እንደማይችል ይጠቁማል፡፡ ቃለ ግጥሙ ሰዎች ለዓለማዊ

ጉዳይ ብቻ ትኩረት በመስጠት ምድራዊ ሕይወታቸውን ከሃይማኖታዊ ሥርዓት ወጣ ባለ መንፈስ እንዳይመሩ የሚሰብክ ከመኾኑም በላይ፣ ሰው በሕይወት በሚኖርበት ጊዜ የሚሠራው ቤት፣ የሚያጠራቅመው ንብረት ምቾትና ተድላ ቀሪና ፈራሽ መኾኑን ይጠቁማል፡፡ በዚኽ ዓለም ላይ የተሠራው ቤት ግድግዳው የረዘመ፣ ባጡ ያማረ፣ ቢኾንም ዐፈር ላይ የተመሠረተ ስለኾነ፣ መፍረሱ አይቀርም የሚል መልእክት አለው፡፡ ከዚኽም በላይ ሰው በዓለም ላይ በሚኖርበት ጊዜ የትዳር ሕይወቱ ያማረ፣ ንብረቱ የዳበረ፣ ገንዘቡ የደለበ፣ ሀብቱ የተከማቸ ቢኾንም ሰው ሟች በመኾኑ ውሎ አድሮ ፈራሽ መኾኑን ወይም በተለያየ ምክንያት የሚጠፋ መኾኑን የሚጠቁም ነው፡፡ የሰማይ ቤት ቢኾን ኖሮ ግን መፍረስ እንደማይችል ይጠቁማል፡፡ በግጥሙ የተላላፈው መልእክትም ሰዎች ለዓለማዊ ኑሮ ትኩረት ብቻ እንዳያደርጉ ቀሪና ፈራሽ ለኾነ ነገር ለምን እንደከማለን ብለው እንዲያስቡ የሚሰብክ ነው፡፡ ሰው በሕይወት ዘመኑ በሚኖርበት ጊዜ የሚያደርገው ነገር ኹሉ ቀሪና ፈራሽ መኾኑን በመገንዘብ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የሚያስችለውን ምግባር እንዲሠራ ይሰብካል፡፡

የሀብተ ሥጋን ቀሪነት ከሚሰብኩ ቃለ ግጥሞች፣ የተለያዩ ሰዎችን ፍጻሜ ሕይወት ለመግለጽ ያገለግላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በአገራችን በተለያዩ የታሪክ ምዕራፎች የመንግሥት አስተዳደርን ወይም አመራርን በበላይነት ለማካኼድ የሚያስችል ሥልጣን የነበራቸውን ሰዎች ስም በመጥራት ፍጻሜ ሕይወታቸው ምን እንደኾነ በቃለ ግጥም እንደሚከተለው ተነገሯል፡፡

ዓለም ዋሾ፣ ዓለም ወረተኛ፣ ዓለም አታላይ፤

ጎንደር ቴዎድሮስ ቤት፣ አልነበርሽም ወይ?

ትግራይ ዮሐንስ ቤት፣ አልነበርሽም ወይ?

ሸዋ ምኒልክ ቤት፣ አልነበርሽም ወይ?

ጎጃም ተክለሃይማኖት ቤት፣ አልነበርሽም ወይ?

ወሎ ሚካኤል ቤት፣ አልነበርሽም ወይ?

ዓለም ዋሾ፣ ዓለም ወረተኛ፣ ዓለም አታላይ፤

ወደ እኛ እንዳትመጪ፤

ከገባሽበት ቤት፣ በደህና ላትወጪ፤

በትልቁ ፋጋ ኩሶ ሳታጠጪ፡፡[12]

ከዚኽ በላይ በተጠቀሱት ስንኞች ከተጠሩት ሰዎች ታሪክና ማንነት መረዳት/መገንዘብ እንደሚቻለው "ዓለም ዋሾ፣ ዓለም ወረተኛ፣ ዓለም አታላይ፤" በሚሉት ሐረጎች የተገለጹት ሐሳቦች፣ ዛሬ ያለ ሥልጣንና ሀብት ለኹልጊዜ፣ ለዘላለም፣ ቋሚ፣ ኗሪ አለመኾናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ ሥልጣን በእጅ፣ ሀብት በቤትና በደጅ በነበሩበት ጊዜ የሚርቁ፣ የሚሸሹ ተደርገው አይታሰቡም፡፡ ጊዜ ተለውጦ፣ ሥልጣንና ሀብት እንዳልነበሩ ሲኾኑ፣ የቀደመ ባለቤታቸውን እንደ አሞኙ፣ እንደ አቄሉና እንደ አጭበረበሩ ይቆጠራሉ፡፡ "አታላይም" ይባላሉ፡፡ በተግባር ያዙበትና ይናዝዙበት የነበረ ሥልጣን፣ በዐይን ያዩትና ይናኙትና የነበረ ሀብት እንዳልበር መኾኑ ድንገት ሲታወቅ ያጣጥሙት የነበረ ድል ሲርቅ እንደ አባይ፣ እንደ ቀጠፊ፣ እንደ ሀሰተኛ ይቆጠራል፤ ቀድሞ "አለኹ" ብሎ፣ ቆይቶ "የለኹም" በማለቱም "ዋሾ" ይባላል፡፡

በቃለ ግጥሙ በተጠቀሱት ሰዎች ዘንድ ሥልጣንና ሀብት ጊዜያዊ ዝምድና ነበራቸው፡፡ ዘውድ ጭነው፣ ዐፄ ተብለው የነገሡት (ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛና ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ) ተክለ ሃይሞኖት፣ ንጉሠ ከፋ ወጎጃምና ሚካኤል፣ ንጉሠ ወሎ ወትግሬ) ጊዜና ታሪክ የፈቀደላቸውን ሥልጣን ተጠቅመው አገር ሕዝብ መርተዋል፡፡ በሥልጣን ተቀናቃኞቻቸው ላይ ድል ተጎናጽፈዋል፡፡ በሀብታቸው የፈለጉትን አድርገዋል፡፡ ሥልጣንም፣ ሀብትም፣ አሸናፊነትም ግን በአንዳቸውም ጸንተው አልቀሩም፡፡ እነዚኽ የጊዜ ሀብቶች ከዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ዐፄ ዮሐንስ፣ በኋላም ከዐፄ ዮሐንስ ወደ ዐፄ ምኒልክ ቤት ኼደዋል፡፡ ተክለ ሃይማኖት "ንጉሠ ጎጃም ወከፋ" ተብለው ገዝተው አልፈዋል፡፡ እንደዚሁም፣ ሚካኤል ንጉሠ ወሎ ወትግሬ[13] ተብለው ገዝተዋል፡፡ ሥልጣንና ሀብት ጊዜ የፈቀደላቸውን ፍቅር ከእያንዳንዳቸው ጋር ፈጽመው ወደ ሌላ ጊዜ ወደ ፈቀደላቸው በመኼዳቸው ወረተኛ ተብለዋል፡፡

በቃለ ግጥሙ በተጠቀሱት ሰዎች ላይ ሥልጣንና ሀብት መጨረሻ "ባለቤት ነን" በሚሉት ሰዎች ላይ ባስከተሉት በደል፣ ጥፋትና ጉዳት ምክንያት ሌሎች ሰዎች ሥልጣንንና ሀብትን አምርረው ስለ መጥላታቸው በመጨረሻዎቹ ሦስት ስንኞች ተገልጸዋል፡፡ የቃለ ግጥሙን ይዘት በአግባቡ ለመረዳት በቃለ ግጥሙ የተጠሩትን ሰዎች ታሪክ በአጭሩ በቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡

---

[12] ጌታሁን ይመር የተባለ ሰው ከምከም ቃሮዳ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤታችን መጥቶ በልቶና ጠጥቶ የስካር ስሜት ላይ ኾኖ የገጠመው ነው፡፡ ዓመተ ምሕረቱንና ቀኑን በትክክል ለማስታዎስ አልተቻለም፡፡

[13] ንጉሥ ሚካኤል ንጉሠ ወሎ ወትግሬ ተብለው ከነገሡ ከአንድ ዓመት በኋላ ጎንደርና ጎጃም ተጨምረውላቸው የወሎ፣ የበጌምድር፣ የጎጃምና የትግራይ ንጉሥ ተብለው ነበር (ምስጋናው ታደሰ፣ 2008፣ 66፤ ባሕሩ ዘውዴ፣ 2008፤ 95)፡፡ በምስጋናው ከተጠቀሱት በተጨማሪ አውሳ አዳል ግዛታቸው እንደ ነበሩ ገልጸዋል፡፡ በጌምድር በማለት ፋንታ ጎንደር ብለው የሚጠሩ አሉ፡፡ ይኽ ግን ስህተት ነው፡፡ በጊዜው ጎንደር የከተማ መጠሪያ እንጂ የግዛት መጠሪያ አልነበረም፡፡

*በመጀመሪያ ቃለ ግጥሙ በሚጠራው ታሪካዊ ዐውድ መሠረት የቴዎድሮስን ማንነትና የሕወት ፍጻሜ እንቃኛለን፡፡ ዓለም ፊቷን ወደ ቴዎድሮስ መቼ መለሰች? መቼስ ፊቷን ከቴዎድሮስ አዞረች? ታሪኩ በአጭሩ የሚከተለው ነው፡፡*

*የቴዎድሮስ የዓለም ስም ካሣ ኃይሉ ነበር፡፡ ካሣ ኃይሉ የዘመነ መሳፍንት የመጨረሻው መሪ በነበሩት ትንሹ ራስ ዓሊ ላይ አመጹ፡፡ ወታደራዊ መቆናጠጫቸውን ቋራ አድርገው ለማጥቃት በዘመቱባቸው የዘመነ መሳፍንት አውራዎች ላይ ተከታታይ ድሎችን አገኙ፡፡ በመጀመሪያ፣ ከራስ ዓሊ ታዞ ሊያጠቃቸው የዘመተባቸውን የጎጃሙን ደጃች ጎሹ፣ ኅዳር ፲፱ ቀን*

*፲፰፻፵፫ ዓ. ም. ጉር ዐምባ ላይ ድል አድርገው ገደሏቸው፡፡ ቀጥለውም፣ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፰፻፵፫ ዓ. ም. የራስ ዓሊን አራት ደጃዝማቾች ጎርጎራ ልዩ ስሙ ብቸኝ በተባለ ሜዳ ላይ አሸነፉ፤ ኹለቱን ደጃዝማቾችም በጦር ሜዳው ላይ ገደሉዋቸው፡፡ የዘመነ መሳፍንቱን የበላይ መሪ ራስ ዓሊን ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፰፻፵፭ ዓ. ም. ፣ አያሻል ላይ ድል አደረጉዋቸው፡፡ ፊታቸውን ወደ ሰሜን አዙረውም፣ የካቲት ፫ ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ. ም. ደረስጌ ላይ ደጃች ውቤ ኃለማርያምን ድል አደረጉ፡፡ ደጃች ውቤ ባሠሯት ደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን "ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" ተብለው ነገሡ፡፡ ከዚኽ በኋላ፣ ወደ ወሎና ሸዋ በመዝመት ለማስገበርና ማዕከላዊ መንግሥት ለመመሥረት እንቅፋት በኾኑባቸው መሳፍንት ላይ ከባድ ክንዳቸውን አሳረፉ፤ ድልም አደረጓቸው፡፡ የሸዋውን መሪ የኃይለ መለኰትን ልጅ ምኒልክን ማርከው ወሰዱ፡፡*

*ይሁን እንጂ፣ የዐፄ ቴዎድሮስን ማዕከላዊ መንግሥት መመሥረት ያልተቀበሉ የጎጃም፣ የበጌምድር፣ የትግራይ፣ የወሎና የሸዋ መሳፍንት በየአካባቢያቸው በየጊዜው በሚያነሡት አመጽ ኃይላቸው ተዳከመ፡፡ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር የፈጠሩት ግጭት የተቃዋሚዎቻቸውን ጎራ አጠናከረው፡፡ በመጀመሪያው ፖለቲካዊና ወታደራዊ እንቅስቃሴአቸው ስድሳ ሺህ ይገመት የነበረው ጦራቸው፣ ወደ ዐሥር ሺህ ዝቅ አለ፡፡ እንቅስቃሴአቸውም በመቅደላ ዐምባ አካባቢ ተገደበ (ባሕሩ ዘውዴ፣ 1999፤ 42)፡፡ ኃይላቸው በደከመበት፣ ግርማቸው በቀነሰበት፣ ጠላታቸው በጎለበተበት፣ የእንግሊዝ ጦር በተቃዋሚያቸው በደጃዝማች ካሣ ምርጫ እየተመራ ወደ መሸጉበት መቅደላ መጣ፡፡ የመሣሪያና የወታደራዊ ሥልጣና ብልጫ የነበረው የእንግሊዝ ጦር በጦርነቱም የረጅም ጊዜ ታማኝ የጦር መሪያቸው ገብርዬ ገደለ፡፡ የፈረጠመ ኃይሉን በደከመ ጉልበታቸው ላይ ሰንዝሮ ታማኝ ወታደሮቻቸውን አጠቃ፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ጠላታቸውን በጦር መሣሪያ ለመከላከል ሞክረው እንደማይችሉ ተገነዘቡ፡፡ በጠላት ጦር ቢማረኩ በአገራቸው ታሪክና በትውልድ ላይ የሚያስከትለውን ጠባሳ የተገነዘቡት ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ሚያዝያ ፯ ቀን ፲፰፻፷ ዓ. ም. በጠላታቸው ላይ ይበረታ በነበረው ክንዳቸው ሽጉጣቸውን ከወገባቸው መዝዘው ራሳቸውን ገደሉ፡፡ ጉሡን አጥቅቶ ዜጎቹን ለማስፈታት የመጣው የእንግሊዝ ጦር የአገር ቅርስ ከመዝረፉም በላይ፣ የዐፄ ቴዎድሮስን ልጅ፣ ልጅ ዓለማየሁ ቴዎድሮስን ይዞ ወደ ህንድ ኼደ፡፡ የዐፄ ቴዎድሮስ ሥልጣነ መንግሥትም እንዲኽ ከኰሶ በሚመር ኹኔታ ተደመደመ፡ ፡ ድል አድራጊነትንና ሥልጣንን ሀብት አድርገው የነበሩት ዐፄ ቴዎድሮስ ፍጻሜ አስከፊነቱ በቃለ ግጥሙ እንደ ተገለጸው መራራ ነው፡፡*

በቃለ ግጥሙ የተጠሩት ደጃዝማች ካሣ ምርጫ በመቅደላ ጦርነት ዋዜማ ላይ እንግሊዞችን ባስተናገዱበት ውለታ ዘመናዊ መሣርያ ከነአሠልጣኙ ስላገኙ ወደ ሥልጣን የሚያደርጉትን ግስጋሴ ለማሳካት አስችሏቸዋል፡፡ ለእህታቸው ለወይዘሮ ድንቅነሽ ምርጫ ባል ለዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ አልገዛም ብለው ሐምሌ 5 ቀን 1963 ዓ. ም. ጦርነት ገጠሙ፡፡ ደጅ አዝማች ካሣ ከእንግሊዞች ባገኙት ዘመናዊ መሣሪያና በእንግሊዛዊው የጦር አማካሪ ኪርክሃም የጦር ስልት ታግዘው አነስተኛ ቁጥር በነበረው ጦራቸው ድል አደረጉ፡፡ ጥር ፲፫ ቀን ፲፰፻፷፬ ዓ. ም. ራሳቸውን "ዮሐንስ አራተኛ" አሰኝተው በአክሱም ከተማ ነገሡ (ባሕሩ ዘውዴ፣ 1999፤ 47)፡፡ በዘመነ መንግሥታቸውም የአገር ውስጥ ተቀናቃኞቻቸውን በኃይልም በድርድርም አስገበሩ፡፡ ከውጭ ኃይሎች ጋር ደግሞ ተደጋጋሚ ጦርነቶችን አካኼዱ፡፡ ድልም አደረጉ፡፡ በራስ አሉላ በሚመራው ጦራቸው ወራሪውን የጣሊያንን ጦር ዶጋሊ ላይ ድል አደረጉ፡፡ ጉንደትና ጉራ ላይ ግብፆትን አሸነፉ፡፡ የግብፅን ጦር ታድጉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሕይወታቸው ያለፈው፣ ሥልጣነ መንግሥታቸውም የተፈጸመው ከድርቡሽ ጋር መተማ ላይ ባደረጉት ጦርንት ነው፡፡ በዚኹ ጦርነት ቅዳሜ መጋቢት ፩ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. ቆሰሉ፡፡ እሑድ መጋቢት ፪ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. በተወለዱ ፶፬ ዓመታቸው፣ በነገሡ በ፲፯ ዓመት አረፉ (ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ 1982)፡፡ የድርቡሽ ጦር ዐንገታቸውን ቆርጦ በመውሰድ ቤተሰቦቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን አሳዘነ፡፡ የታሪካቸውም ፍጻሜ በአገር ላይ ትልቅ ጠባሳ ጥሎ አለፈ፡፡

በግጥሙ የተጠሩት ምኒልክ ኅዳር ፲፰፻፵፯ ዓ. ም. በቴዎድሮስ ተማርከው ከሸዋ ወደ ጎንደር ተወሰዱ፡፡ በ፲፰፻፶፯ ዓ. ም. ከመቅደላ አምልጠው ወደ አባታቸው የትውልድ ቦታ ወደ ሸዋ መጡ፡፡ በጊዜው ሸዋን ያስተዳድር የነበረውን አቶ በዛብህን በጦርነት አሸንፈው አንኰበር ገብተው የሸዋ ንጉሥ ተባሉ፡፡ በ፲፰፻፷ ዓ. ም. የዐፄ ቴወድሮስን ሞት እንደሰሙ፣ "ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፣ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት" የሚል ማኅተም አሠርተው ካገር ውስጥም ከውጭም አገር መሪዎች ጋርም ይጻጻፉ ጀመር፡፡ ይሁን እንጂ፣ መጋቢት ፲፪ ቀን ፲፰፻፸ ዓ. ም. በዐፄ ዮሐንስና በምኒልክ መካከል ስምምነት ተደረገ፡፡ ከስምምነቶቹ መካከል፣ ምኒልክ "ንጉሠ ነገሥት ነኝ" ማለታቸውን እንዲተውና በሸዋ ንጉሥነታቸው እንዲጠኑ ኾነ፡፡ ምኒልክ በ፲፰፻፷፰ ዓመተ ምሕረት በዐፄ ዮሐንስ የሚደገፈውን አባ ዋጠውን አስረውም መሐመድ ዓሊን የወሎ ጠቅላይ ገዥ አድርገው የሾሙበት ግዛታቸው ለዐፄ ዮሐንስ እንዲኾን አደረጉ፡፡ ንጉሥ ምኒልክም የሰሜን ግዛታቸውን ሲያጡ ፊታቸውን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ አዞሩ፡፡ የማስገበር ዘመቻዎችን በተከታታይ በማካኼድ ደቡብ ኢትዮጵያን አስገበሩ፡፡

ዐፄ ዮሐንስ መተማ ላይ ከሞቱ በኋላ፣ ብቸኛው ወራሴ መንግሥት ኾኑ፡፡ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፰፻፹፪ ዓ. ም. ቅብዐ መንግሥት ተቀብተው ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ፡፡ ዙሪያውን የከበቧቸው፣ የጣሊያን፣ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ቅኝ ገዥ መንግሥታን ሤራዎች ተቋቁመው፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለመጠበቅ ብዙ ታገሉ፡፡ በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. ጣሊያን የሰነዘረችባቸውን ጥቃት ዐድዋ ላይ ድል በማድረግ በቅኝ ግዛት ሥር ለነበሩ አገሮች ኹሉ ለነጻነት የማንቂያ ደወል ደወሉ፡፡ "ከዐድዋ ድል በኋላ፣ ዙሪያውን ከከበቧት የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎች ጋር በተደረገው የደንበር መካለል ስምምነትም ዓለም አቀፋዊ ሰውነቷን አገኘች" (ባሕሩ ዘውዴ፣ 1999፤ 66)፡፡

ይሁን እንጂ፣ በ፲፱፻ ዓ. ም. በድንገት በመታመማቸው ዐደባባይ መውጣትም በግብር አዳራሽ መቀመጥም ተሳናቸው፡፡ በ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርደው የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ጠበል ጠጥተው እንደ ተሻላቸው ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ (፲፱፻፶፱፤ ፫፻፵) ቢዘግቡም፣ በተሟላ ጤንነት አገራቸውንና ሕዝባቸውን መምራት አልቻሉም፡፡ በፈረጠመ ጉልበትና በሚደመጥ አንደበት አገራቸውን መምራት እንደማይችሉ በመገንዘባቸው፣ ወራሴ መንግሥታቸው የልጅ ልጃቸው አቤቶ ኢያሱ መኾናቸውን ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፩ ዓ. ም. ለሕዝባቸው በዐዋጅ አሳወቁ፡፡ "ከስድስት ዓመት በላይ ታመው የቆዩት ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ፣

ተኅሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፮ ዓ. ም. ሞቱ፤ የመሞታቸው ወሬ ሕዝቡን ያሸብራል ተብሎ ስለ ተሠጋ ወሬው ተደብቆ በቤተ መንግሥታቸው አጠገብ በምትገኝ በሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ተቀበሩ፡፡ የመንግሥቱም አስተዳደር እንደ ቀድሞው በዳግማዊ ምኒልክ ስም ይካሄድ ነበር"፡፡ የዐፄ ምኒልክ መሞት በይፋ የተገለጸውና ኀዘን የተደረገው፣ መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፱ ዓ. ም. ልጅ ኢያሱ ተሽረው ከመንግሥት ሥልጣን በወጡ ጊዜ ነው (ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ፣ ፲፱፻፶፱፤ መቅድም)፡፡

በጊዜው የዐፄ ምኒልክ ሞት እንደ ተሰማ፣ በይፋ ኀዘን አለመደረጉ ቤተሰቦቻቸውን እንደጎዳ፣ ድርጊቱም ሃይማኖታዊ ሥርዓት እንዳልሆነ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፱ ዓ .ም. ባደረጉት ንግግር ገልጸዋል፡፡ በንግግራቸውም፣ "ምኒልክን ያህል ንጉሥ ፍታት ሳይደረግላቸው እንደቆዩ፣ እርሳቸውም በአባታቸው ሞት የተሰማቸውን ኀዘን ለመግለጽ እንዳልቻሉና የአባታቸውን ሬሣ ከሁለት ዓመት በላይ ታቅፈው እንደኖሩ አምርረውና ቅዱሳን መጻሕፍትን አጣቅሰው ተናገሩ፡፡" (ባሕሩ ዘውዴ፣ 2008፤ 191)

በቃለ ግጥሙ የተጠሩትና ፍጻሜአቸው ያላማረላቸው ንጉሥ ሚካኤል[14] ክርስትና ከመነሣታቸው በፊት ስማቸው መሐመድ ዓሊ ነበር፡፡ አባታቸው ዓሊ የኢማም ሊበን፣ ማመዶች በመባል የሚታወቀውን ሥልጣነ ዘር ሐረግ የመሠረቱ ናቸው፡፡ መሐመድ ዓሊ 18 ዓመት ሲኾናቸው በልጅነታቸው የሞቱትን የአባታቸው የዓሊ ሊበን ሥልጣን ለእኔ ይገባል በማለት የራሳቸው ወገን ከኾኑት ከአመዴ ሊበን (አባ ዋጠው) ጋር ተጋጩ፡፡ አባ ዋጠው አነስተኛ ግዛት በመስጠት ሊደልሏቸው ሞከሩ፡፡ መደለያውን ያልተቀበሉት መሐመድ ዓሊ ሸሽተው ድጋፍ ለማግኘት ለዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ገቡላቸው፡፡

ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ከትግራዩ በዝብዝ ካሣ ጋር ሲዋጉ መሐመድ ዓሊም ከንጉሡ ጎን ተሰልፈው ተዋግተዋል፡፡ በጦርነቱም በዝብዝ ካሣ ሲያሸንፉ መሐመድ ዓሊን በቁጥጥር ሥር አውለው አሰሯቸው፡፡ ነገር ግን፣ መሐመድ ዓሊን ከማሰር ይልቅ ወደፊት ወሎን ለመቆጣጠር በሚደረገው ሂደት ሊኖራቸው የሚችለውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከእስር ፈትተው የተወሰነ ጦር ሰጥው ደጃዝማች ተሰማ ከተባሉ የጦር መሪ ጋር ወደ ወሎ ላኳቸው፡፡

---

[14] የንጉሥ ሚካኤል ታሪክ በአብዛኛው የተወሰደው ከምስጋናው ታደሰ (2008)፤ እንዲሁም ከባሕሩ ዘውዴ (2008) ነው፡፡

የመሐመድ ዓሊና የደጃዝማች ተሰማ ጥምር ጦር ወደ ወረሂመኖ በመግባት ሥልጣኑን በጊዜያዊነት ከያዘው ከዓሊ መስተዋት ጋር ተዋግተውና አሸንፈው ዋና ከተማዋን ተንታን ተቆጣጠሩ፡፡

በድርጊቱ የተቆጡት የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ አባ ዋጠውን ከእስር ፈትተው በወሎ ላይ እንደገና ሾመው ላኳቸው፡፡ ከእስር የተፈቱት አባ ዋጠው፣ መሐመድ ዓሊን ወግተው በማሸነፍ ንጉሥ ምኒልክን በመክዳት ራሳቸውን ነፃ የማመዶች ኢማም በማለት አወጁ፡፡ መሐመድ ዓሊም ወዳጃቸው ዐፄ ዮሐንስ ሊደርሱላቸው ባለመቻላቸው ከሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ጋር አጋርነት በመፍጠር አባ ዋጠውን ወግተው በማሸነፍ አሠራቸው፡፡ “ንጉሥ ምኒልክም መሐመድ ዓሊን የወሎ ኢማምነት በዐዋጅ ሰጥተው” ከዋደት እስከ በሸሎ፣ ከዐባይ እስከ አዛሎ በተዘረጋው የወሎ ክፍለ ሀገር ላይ ሾሚቸው፡፡ ነገር ግን፣ መሐመድ ዓሊ በተሾሙ ባሙቱ ምኒልክን ከድተው ከምኒልክ ጋር ግጭት ላይ የነበሩትን ወይዘሮ ባፈናን በመደገፍ የወረኢሉን ከተማ አቃጥለው ሸፈቱ፡፡ መሐመድ ዓሊ ባመፁባቸው ጊዜ ምኒልክ አባ ዋጠውን ከእስር ፈትተው እንደገና በወሎ ላይ በመሾማቸው በሁለቱ የማመዶች ልዑላን ተቀናቃኞች መካከል የሥልጣን ትግሉ ቀጠለ፡፡ መሐመድ ዓሊም ምኒልክን ለማስገበር ከትግራይ ወደ ሸዋ እየገሰገሱ ከነበሩት ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ልቼ ላይ ተቀላቀሉ፡፡ የአባ ዋጠውና የመሐመድ ዓሊ የሥልጣን ሽኩቻ በቦሩ ሜዳው በተደረገው የሃይማኖት ጉባዔ ፍጻሜውን አገኘ፡፡

በ1870 ዓ. ም. ቦሩ ሜዳ ላይ በተካሄደው የሃይማኖት ጉባዔ ኢማም መሐመድ ዓሊ ሃይማኖታቸውን ወደ ክርስቲያንነት ቀየሩ፡፡ ከቦሩ ሜዳ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኘው በጎልቦ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በመጠመቃቸው የክርስትና ስማቸው ሚካኤል ተባለ፡፡ የክርስትና አባታቸው ዐፄ ዮሐንስም የራስነት ማዕረግ ሰጥተው በምዕራቡ የወሎ ክፍለ ሀገር ላይ ገዥነት ሾሚቸው፡፡ ራስ ሚካኤልም ከአስተዳደር ሥራ እስከ ጦር ግንባር ድረስ ይሠጧቸው የነበሩ ኃላፊነቶችን በአግባቡ ተወጥተዋል፡፡ ራስ ሚካኤል ከዐፄ ዮሐንስ ጋር መጀመሪያ ሰሐጢ ዘምተዋል፡፡ በኋላም መተማ ዘምተው ከድርቡሽ ጋር ተዋግተዋል፡፡

የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ከነገሡ በኋላም የቅርብ አጋዣቸውና አገልጋያቸው በመኾን በሀገሪቱ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የሚሰጧቸውን በርካታ ኃላፊነቶች በአግባቡ ተወጥተዋል፡፡ ለዐፄ ምኒልክ በነበራቸው ታማኝነት ልጃቸውን ሸዋ ረጋ ምኒልክን አግብተው ወዳጅነታቸውን በጋብቻ አጽንተዋል፡፡ ከዐፄ ምኒልክ ጋር ዘምተውም ህዳር 28 ቀን 1888 አምባላጌ ላይ፣ የካቲት 23 ቀን 1888 አድዋ ላይ ከኢጣሊያ ጋር ተዋግተዋል፡፡ የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ጤንነት ታውኮ ሥልጣናቸው ወደ ልጅ ልጃቸው በመዛወሩ ያኮርፋሉ የተባሉት ራስ ወሌ በአንኰበር እንዲታሰሩ ሲደረግ ግዛታቸው የነበረው የጁ በራስ ሚካኤል እንዲተዳደር ተደረገ፡፡

ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽ ሆነው ከተሾሙ በኋላ የሚካኤል ሥልጣንና ሃይል ከሙቼውም ጊዜ በላይ እየጨመረ መጣ፡፡ በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ለምና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰው እስከመሆን ደረሱ፡፡ ልጅ ኢያሱን ከሥልጣኑ ለማውረድ በተደረገው ሙከራ አስተባባሪዋል ተብለው የተጠረጠሩትን ራስ አባተ ቧ ያለውን ከከምባታ ወደ አዲስ አበባ አስጠርተው በቁጥጥር ሥር አውለው ወደ ወሎ በመውሰድ በመቅደላ አምባ ላይ እንዲታሰሩ አድርገዋል፡፡

ዐፄ ምኒልክ ማረፋቸው ይፋ ከተደረገ በኋላም ራስ ሚካኤል ግንቦት 23 ቀን 1906 ዓ. ም. በግብፃዊው ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ እጅ ተቀብተው "ሚካኤል ንጉሠ ወሎ ወትግሬ" ተብለው ዘውድ ጭነው በነገሡበት ዕለት ለዐምሥት ደጃዝማቾች የራስነት ማዕረግ ሰጥተዋል፡፡ ከአንድ ዓመት በኋላ ጎንደርና ጎጃም ተጨምረውላቸው የወሎ፣ የትግራይ፣ የጎንደርና የጎጃም ንጉሥ ሆነዋል፡፡ በሀገሪቱ በርካታ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ቁልፍ ሚና ስለ ነበራቸው ብዙዎቹ የኢያሱ ውሳኔዎች በንጉሥ ሚካኤል የተቃኙ ነበሩ ይታወቃል፡፡ ንጉሥ ሚካኤል ከአውሮጳ ሀገሮች

በተለይም ከጀርመን ጋር ግንኙነት መፍጠር ችለው ነበር፡፡ በወቅቱም የጀርመኑ ዲፕሎማት ሎሬንዝ ጆነሰን መቀመጫውን ደሴ ላይ አድርጎ ነበር፡፡ በጀርመን ኢምባሲ በአስተርጓሚነት ሲያገለግሉ የነበሩት ከንቲባ ገብሩም በንጉሥ ሚካኤል ትዕዛዝ ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ በመዛወር የንጉሡ አስተርጓሚ ሆነው እንዲያገለግሉ ተመድበው ነበር፡፡

ይሁን እንጂ፣ የልጅ ልጃቸው ልጅ ኢያሱ በሸዋ መሳፍንትና መኳንንት ከሥልጣን እንዲወርድ በመደረጉ አኮረፉ፡፡ የሸዋን አድማ በጦር ፈትተው ልጅ ኢያሱን ወደ ሥልጣን ለመመለስ ወደ ሸዋ ዘመቱ፡፡ ቶራ መስክ ላይ በተደረገው የመጀመሪያው ውጊያ ድል ቀናቸው፡፡ ሰገሌ ላይ ጥቅምት 17 ቀን 1909 ዓ. ም. በተደረገው ጦርነት ተሸንፈው ተማረኩ (ባሕሩ ዘውዴ፣ 1999፤ 139)፡፡ ከጦርነቱ በፊት በፈረስ ስማቸው "ሻንቆ ምን አለ?" "እየቆራረጥክ ስቀለው አለ፡፡" እየተባለ ሲጨፈር የነበረው፣ ከተማረኩ በኋላ "ሻንቆ ምን አለ?" "የአምላክ ታምሩ ብዙ ነው አለ፡፡" ተባለ፡፡ የኸም የንጉሥ ሚካኤልን የወደፊት ዕጣ ፈንታ አመልካች ነበር፡፡

ተማራኪው ንጉሥ ሚካኤል፣ ለአንድ ሳምንት አዲስ አበባ በሀብተ ጊዮርጊስ ቤት ከቆዩ በኋላ በዝዋይ ሐይቅ ደሴት ውስጥ በግዞት ታሰሩ፡፡ ነገር ግን ለጤናቸው ስለአልተስማማቸው ለንግሥት ዘውዲቱና ለዐልጋ ወራሽ አመልክተው ሆለታ ወደሚገኘው የዐፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥት እንዲዛወሩ ተደረገ፡፡ ለኹለት ዓመታት ከዐሥር ወር ከ18 ቀናት በግዞት ከቆዩ በኋላ ጳጉሜ 3 ቀን 1911 ዓ. ም. ዐርፈው በሆለታ መድኀኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ፡፡ ካረፉ ከዐሥር ዓመት በኋላ በ1921 ዓ. ም. አጽማቸው በተንታ ሚካኤል እንዲያርፍ ተደረገ፡፡ (ምስጋናው ታደሰ፣ 2008፤ 101-102) መጨረሻቸው በኀዘንና በትካዜ አለፈ፡፡ ዘመድ ወዳጅን ለመረረ ኀዘን ዳርጎ አለፈ

**፰) ማጠቃለያ**

የሰው ልጅ ፈቃደ ሥጋውን ለጥቂት ዓመታት እየፈጸመ ከኖረ በኋላ፣ ሞተ ሥጋ እንደማይቀርለት በዐማርኛ ቃለ ግጥሞች ይገለጻል፡፡ ሞት ዘገየም ፈጠነ የኹሉም ሰው ዕጣ ፈንታ መኾኑን በቃለ ግጥሞች ይሰበካል፡፡ የሰው ልጅ ከሥጋ ሞት በኋላ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ይወርስ ዘንድ በሕይወተ ሥጋ እያለ ለሕይወተ ነፍስ እንዲተጋ ቃለ ግጥሞቹ ይመክራሉ፡፡

የሰው ልጅ በሕይወተ ሥጋ በሚኖርበት ጊዜ ለሥጋው ምቾትና ድሎት የሚሰጡትንና ሥጋዊ እርካታ የሚያገኝባቸውን ጉዳዮች ለማግኘት መጓጓቱና ማግኘቱ ጥቅም እንደሌለው በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚሰብኩ ቃለ ግጥሞች በርካታ ናቸው፡፡ ቃለ ግጥሞቹ ሰው የዓለምን ኑሮ እንዲንቅና እንዲተው፣ መንግሥተ ሰማይን ለመውረስ እንዲችል የሚቀሰቅሱ ናቸው፡፡ የሚያስችለውን መንገድ እንዲከተል ይቀሰቅሳሉ፤ ይሰብካሉ፡፡

የዓለምን ከንቱነትና የሞተ ሥጋ አይቀሬነትን የሚያስረዱና ከኹለተኛ ሞት ለመዳን ዓለምንና በውስጡ ያለውን ኹሉ የሰው ልጅ እንዲንቅና ከሕግ የወጣ ክፉ ሥራ እንዳይሠራ የሚሰብኩ የዐማርኛ ቃለ ግጥሞች በኅብረተ ሰቡ ዘንድ በደስታና በኀዘን አጋጣሚዎች በልዩ ልዩ መንገድ ይቀርባሉ፡፡ የዚኽ ዓይነቱን ሃይማኖታዊ ምክር በግጥም መልክ (በኅብር ቅኔ ዓይነት) አያዘጋጁ በሊቀ መኳሶች (አዝማሪዎች) አንደበት በጥዑም ዜማ አማካይነት ለምእመናን ጆሮ እንዲደርስ ሲያደርጉ የነበሩት ከመሠረቱ ወይም ከጅምሩ የሃይማኖት ሊቃውንት ነበሩ፡፡ እኒኽ ሊቃውንት ዓላማቸው የሃይማኖት ትምህርት በአግባቡ የማያገኙትን ምእመናን እያዋዙ ማስተማር በመኾኑ በቀላሉ ወደ ልቦና ሰርጾ በሚገባና ለወንጌል ትምህርት ማስተማሪያ አመቺ በኾነ መንገድ እንዲኽ ዓይነቱን ድርሰት ለስብከታቸው ማስተላለፊያ ይጠቀማሉ፡፡ መንፈሳዊ ይዘት ያላቸውን ቃለ ግጥሞች ትኩረት ሰጥቶ ማጥናት በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ምን ያኽል እንደሰረጸ ለመረዳት ያስችላል፡፡ እናም ትኩረት ሰጥቶ ማጥናት አስፈላጊ መኾኑን የሚመለከታቸው ኹሉ ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

**መረጃ ጽሑፎች**


ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፡፡ ፲፱፻፷፩፡፡ *ዝክረ ነገር*፡፡ አዲስ አበባ፤ ሴንተራል ማተሚያ ቤት፡፡

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፡፡ ፲፱፻፶፱፡፡ *አማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው* ፡፡ (፪ኛ ዕትም) አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ምስጋናው ታደሰ፡፡ 2008፡፡ *ሚካኤል ንጉሥ ወሎ ወትግሬ*፡፡ አደስ አበባ (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፡፡

ሰይፉ መታፈሪያ፡፡ 1993 (እ.ኤ.አ)፡፡ "የፎክሎር መዝገበ ቃላት ጥንቀራ ቅድመ-ዝግጅት"፡፡ የኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት JOURNAL OF ETHIOPIAN STUDIES. Vol. XXVI, No. 1, pp. 73 - 116.

ሥርገው ሐብለ ስላሴ፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ የአዲሱ ሥልጣኔ መሥራች፡፡ (ዓመተ ምሕረቱ፣ የታተመበት ቦታና አሳታሚው አልተገለጹም፡፡

ሥርግው ገላው (ሐተታ)፡፡ 2002፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ [ተክለ ኢየሱስ እንደጻፈው]፡፡* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ባሕሩ ዘውዴ፡፡ 2008፡፡ *ሀብቴ አባ መላ፤ ከጦር ምርኮኛነት እስከ አገር መሪነት*፡፡ አዲስ አበባ፤ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፡፡

ባሕሩ ዘውዴ፡፡ 1999፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983*፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፡፡ ፲፱፻፶፩፡፡ *ከሣቴ ብርሃንና ተሰማ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ተሾመ ይመር አበባው፡፡ 1997 (እ.አ.አ)፡፡ "የአማርኛ ግጥሞች"፤ የኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት JOURNAL OF ETHIOPIAN STUDIES. Vol. XXX, No. 1, pp. 89- 123.

ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ፡፡ 2002፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ* ፡፡ (ሐተታና አርትኦት ሥርግው ገላው) አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ 1982፡፡ *ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት*፡፡ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት (ቦሌ ማተሚያ ቤት)፡፡

ተገኝ ተአምሩ (አለቃ)፡፡ ፲፱፻፷፩፡፡ *ያማርኛ ሐረግ በቅኔዎች ሕግ፡፡* (አዲስ አበባ?) ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ንጉሴ ነገዎ ደጋጋ፡፡ 1992፡፡ *የቅኔ አፈታት ዘዴዎችና የምርጥ ቅኔዎች ስብስብ*፡ (አዲስ አበባ?) ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፡፡

ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ ፲፱፻፹፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት* ፡፡ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ ፲፱፻፸፪፡፡ *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት*፡ (፩ኛ ዕትም) አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ ፲፱፻፺፭፡፡ *የግእዝ ቅኔያት፣ የሥነ ጥበብ ቅርስ ሦስተኛ መጽሐፍ*፡ አዲስ አበባ፤ (የማተሚያ ቤቱ ስም አልተገለጸም)፡፡

ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ ፲፱፻፺፫፡፡ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፡፡ ፲፱፻፷፪፡፡ *ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው*፡፡ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ቤት፡፡

ዓለማየሁ ሞገስ፡፡ ፲፱፻፷፯፡፡ *የአማርኛ ሐረግ*፡ (አዲስ አበባ?) ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ዓለማየሁ ሞገስ፡፡ ፲፱፻፵፬፡፡ *የአማርኛ ግጥምና ቅኔ፤ ማስተማሪያ*፡ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም የቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

ይኄይስ ወርቄ (መምህር)፡፡ “ንባብ ወትርጓሜ ዘቅኔያት፡፡ እዕማደ ምሥጢራት”፡፡ *የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት Journal of Ethiopian Studies. Haile Selassie I University Institute of Ethiopian Studies, Vol. VI, No.2,* 1968, PP. *119-217.*

ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ ፲፱፻፷፪፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፡ (አዲስ አበባ?) አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ደበበ ኃይለጊዮርጊስ፡፡ 2008፡፡ *አዲሱ የአማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው* ፡፡ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ (ጸሐፊ ትእዛዝ)፡፡ ፲፱፻፵፱፡፡ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ* ፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ጎሹ ሞገስ፡፡ 1964፡፡ “የአማርኛ የልመና ግጥሞች”፡፡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ዲግዕ)፡፡

Mesfin Messele. 2000. "Abbawudde Oral Poetry in South Wollo: A Descriptive Analysis." Addis Ababa University: Institute of Language Studies, Department of Foreign Languages.